# ዓባይ

ዓባይ 8ኛ ዓመት; ቁጥር 6 የተማሪዎች የምረቃ በዓል ልዩ ዕትም ነሐሴ 2014 ዓ.ም

www.bdu.edu.et




## እንኳን ለ2014 ዓ.ም የተማሪዎች የምረቃ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

## በውስጥ ገፆች

ርዕሰ አንቀጽ ------------------------------------------------ገጽ 3

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት መልዕክት-------------ገጽ 4

የኢንፎ/ስት/ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት መልዕክት-------ገጽ 5

የሬጅስትራርና አልሙናይ ማኔጅመንት ዳይሬክተር መልዕክት----- ገጽ 5

የተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ--------------------------ገጽ 6-15

### መለስተኛ ማሻሻያ ተደረገ

በዩኒቨርሲቲያችን የውስጥ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በየወሩ እየታተመች የዩኒቨርሲቲያችን ልሳን በመሆን ለደንበኞቻችን መረጃና ሃሳብ የምታደርሰዋ ናይል ጋዜጣ መለስተኛ የቅርጽና የይዘት ማሻሻያ ተደርጎባት መታተሟን ቀጥላለች፡፡

በመሆኑም ከባለሙያዎች በተሰጠ አስተያየትና ከአንባቢያን በደረሰን ምክር የፊት ገጽ መለስተኛ ማሻሻያ በማድረግ ናይል ይባል የነበረው መጠሪያ ከውጭ ቋንቋ የመጣ በመሆኑ ወደ የአገር ውስጥ ቃል በመቀየር ዓባይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ ጋዜጣ ከዓባይ 8ኛ ዓመት ቁጥር 4 ሰኔ 2014 ዓ/ም ጀምሮ ናይል የሚለው ቀርቶ ዓባይ በሚል አዲስ መጠሪያ በመያዝ መታተሟን ቀጥላለች፡፡

ዓባይ Nile

በ2006ዓ/ም ተመሰረተ::

ዓባይ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት እየተዘጋጀ የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ፤

## ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ!

**ዋና አዘጋጅ**
ግርማው አሸብር
girmawashebir@gmail.com

**ም/ዋና አዘጋጅ**
አለባቸው አለሙ
aalemu45@gmail.com

**ፎቶ ግራፍ**
ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ
አገሬ ዘለቀ

**ስርጭት**
አልማዝ አምበሉ
ኑኑሸት ምትኩ
ትርንጎ ወለላው
ወርቅነሽ አበባው
ቀራለም አድማሱ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ቤተልሄም ወርቅነህ
አለባቸው አለሙ
አገሬ ዘለቀ

**ፀሀፊ**
አበባ ካሳው
መልሰው አደመ

**ዘገባ**
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ
ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ሸጋው መስፍን
ባንቹ ታረቀኝ

**ሾፌር**
ፈንታሁን አንሙት
ላመስግን ጫኔ

**አድራሻ፡-** ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ባሕር ዳር ጥበብ ህንፃ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512
ፖ.ሳ.ቁ 79
ስ.ቁ +251 58 3206059

አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ፤ ሰኔ 2014 ዓ/ም

## Motto:

Wisdom at the source of the Blue Nile

## Vision:

BDU aspires to be of the leading research—in tensive Universities in Africa and the first choice in Ethiopia by 2030.

## Mission;

Promote advanced research and innovation on the basis of the country's requirements;
Produce graduates with relevant professions and necessary competences (knowledge, skills and attitude) to respond to the national labor market requirement to eventually ascertain the global competitiveness of the country;
Improve lives through evidence-based and transformative community engagement;
Enhance demand-driven and problem solving technology transfer.



# ርዕሰ-አንቀጽ

## ዩኒቨርሲቲ የቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን የህይወት ትምህርት ቤትም ነው

በአገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረበት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የግልና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር ከፍ እያለ መጥቷል፡፡ በዚህም በርካታ ዜጎች ቀለም ከመቁጠር እስከ ፍልስፍና ዲግሪ ባለቤት የመሆን እድሉን አግኝተዋል፡፡ በዚህ ውስጥም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፣የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ስለተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ የሚመራመሩ ባለሙያዎችን ከእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ማፍራት ተችሏል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም በ1950ዎቹ አጋማሽ አካባቢ በቴክኖሎጂ ዘርፍ ተመስርቶ ዛሬ ላይ በአያሌ የእውቀት አይነቶች ለዜጎች ትምህርትና ስልጠና እየሰጠ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ሂደት ዩኒቨርሲቲ ትምህርትን ለመቅሰም ከተለያዩ አካባቢዎች የነገ ሃገር ተረካቢ ወጣቶች ከየአካባቢያቸው ከሚገኙ 2ኛ እና መሰናዶ ት/ቤቶች ወደ ዩኒቨርሲቲ ይገባሉ፡፡ አብሮ መኖርን፣ የተለያየ ማንነት መተዋወቅን ፣ ከቤተሰብ ተነጥሎ መኖርን፣ ውድድርና ፉክክርን፣ ውድቀትና ስኬትን ማየት ይጀምራሉ፡፡ በውስጡም ተዋናዮች ሆነው ያልፋሉ፡፡ በመጀመሪያ ከቤተሰብ ተነጥሎ መኖርን፣ ቀጥሎ የህይዎት መንገድን በራስ መወሰንን ይለማመዳሉ፡፡

በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከአስተማሪዎቻቸው ከሚሰጣቸው የቀለም ትምህርት በስተቀር በግል ህይወታቸው በ ኩል ብቸኛው ውሳኔ ሰጪ የመሆን እድል ያገኛሉ፡፡ ይህ እድል መልካምም ሆነ መጥፎ አጋጣሚን ሊያመጣ ይችላል፡፡ በተለይ የመጀመሪያ ዲግሪ አፍላ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በጓደኛ መረጣ፣ የቀን ተቀን ውሎ፣ የንባብ ባሕል፣ ጊዜ አጠቃቀም እና ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ራሳቸውን ፈልገው የሚያገኙበት ወይም ራሳቸውን ረስተው የሚያጠፉበት ሁለት ምርጫ ውስጥ ነው የሚወድቁት፡፡ ይህ አጋጣሚ በዩኒቨርሲቲ ህይወት ውስጥ ከቀለም ትምህርትን ቀስሞ ከመመረቅ በላይ ከህይወት መመረቅን ጭምር የሚጠይቅ ነው፡፡ አበው ‹‹ሰው ከፊደል ሀ ብሎ፤ ከመከራ ዋ ብሎ ይማራል›› የሚሉት አባባል እንደሚያስረዳው ይህ አባባል በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ጥሩ ምሳሌ መሆን ይችላል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሚያጋጥሟቸው አዳዲስ የህይወት መሰናክሎችና መልካም እድሎች ራሳቸውን በሁለት በኩል የተሳሉ ሆነውና በስለው እንዲመረቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ አይነቱ ምረቃ የሚገኘው በመደበኛነት ከዩኒቨርሲቲ ከሚሰጠው የቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከሚያጋጥም የህይወት ልምድ ጭምር ነው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2014 ዓ/ም በመደበኛ የቀለም ትምህርት በዩኒቨርሲቲው ከ3 እስከ 7 ዓመታት በግቢ ውስጥ ህይወታቸው የበቁ ተማሪዎችን ነሐሴ 21/2014 ዓ/ም ያስመርቃል፡፡

በህይወታችሁ ደግና ክፉ በመለየት፣ ራስን ማስተዳደርና መምራት፣ ውሳኔ ሰጭነትና የኑሮ ዘዴን ዘይቤ ለይታችሁ እና ተለማምዳችሁ እየተመረቃችሁ ነው፡፡ በግቢ ውስጥ በህይወት ልምዳችሁና በቀለም ትምህርታችሁ ለቀረቡላችሁ ፈተናዎች እውነትና ውሸቱን ለይተው፣ መልካሙን ነገር መርጠው፣ ጥሩውን ከጥሩ፣ እኩይውን ከእኩይ አዛምደው ይህም በአስተማሪዎቻቸው እርምት ተደርጎበት በቂ ውጤት በማግኘት እየተመረቃችሁ ነው፡፡ የአስተማሪው እርማት የውጤት መጠንን መቀነስና መጨመር ላይ የተወሰነ ሲሆን ድምር ውጤቱ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ማሳለፍ ወይም ከትምህርት ገበታ ማባረር ይሆናል፡፡ ከምረቃ በኋላ የሚያጋጥሙ ፈተናዎች ግን ከዩኒቨርሲቲ ፈተናዎች የተለዩ ናቸው፡፡

በዚህ መልኩ የሚያጋጥም ልክነትና ስህተትነት የእርማታቸው ውጤት ክብርና ውርደት ነው፡፡ በዚህ በኩል ሁሉም ፈታኝ እና አራሚ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በግቢ ውስጥ የተገኘው የህይወት ትምህርት ከግቢ ውጭ ለሚያጋጥም ፈተና መውጫ እና የክብር ባለቤት እንዲያደርጋችሁ የዓባይ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ይመኝላችኋል፡፡



**ፍሬው ተገኘ (ዶ/ር)**
**የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት**

ውድ ተመራቂዎች:-
ይህ የምረቃ ሥርዓት እና ውጤቱ የሆነው ልዩ የደስታ ስሜት በሕይወት ዘመናችሁም ኹሉ ልዩ ትዝታ ስለሚሆን እንኳን ደስ አላችሁ! ይልቁንም የዩኒቨርሲቲያችንን 60ኛ ዓመት አልማዝ ኢዮቤልዩ የምሥረታ በዓልን ለማክበር ባለንበት የዋዜማ ዝግጅት ላይ በመሆናችን እንኳን ደስ አላችሁ!

ዩኒቨርሲቲውን ለ60ኛ ዓመት ያበቃው እና ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ከመሠረቱት ሁለት አንጋፋ ተቋማት አንዱ የዚያኔው ባሕር ዳር ፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት ሲሆን ዛሬ ላይ ባሕር ዳር የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በዓለም አቀፍ ደረጃ ABET (Accreditation Board for Engineering and Technology) በሚባል በአሜሪካ ውስጥ በሚገኝ ድርጅት አራቱን የምህንድስና ፕሮግራሞች (ኬሚካል፣ ሲቪል፣ ኤሌክትሪካል እና ሜካኒካል) ዕውቅና ለማስጠት የመጀመሪያውን ማጣሪያ አልፎ የ2ኛውን እና የመጨረሻውን ዙር በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። ይህ ውጤት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች የመጀመሪያ ዩኒቨርሲቲ ያደርገዋል።

የኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሁለት ቤተ-ሙከራዎችን በ15 መለኪያዎች ዕውቅና በማስጠት እና የማስተማሪያ ፋብሪካ (Learning Factory) ጽንሰ ሀሳብን በመተግበር በአገሪቱ ግንባር-ቀደም ነው። ለዚህም ይመስላል ከኢንስቲትዩቱ ምሩቃን ከ25 በመቶ በላይ የራሳቸውን ሥራ የሚፈጥሩት። እነዚህንና ሌሎችን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መልካም ተመክሮዎች በሁሉም አካዳሚክ ክፍሎች ለማሟላት እየተሠራ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው 50 ዓመት ባስቆጠረው እና ለሀገር በተረፈው የፔዳኮጂ ዕሴቱ የታገዘ ትምህርት በመስጠት ይታወቃል። እናንተ የዛሬ ተመራቂዎች የዚህ ልዩ ዩኒቨርሲቲ ምሩቃን በመሆናችሁ በራሳችሁ ልትተማመኑ ይገባል።

ውድ ተመራቂዎች:-
የተማሪነት ሕይወት በብዙ ፈተናዎች ውስጥ የሚታለፍ ለመሆኑ ራሳችሁ ምስክር ናችሁ። የድል አክሊላት፣ የወርቅ ሽልማት፣ የአሸናፊነት ዋንጫዎች፣ የጀግንነት ኒሻኖች፣ ውድ የሆኑ ማእድናት፣ የምድር በረከቶች፣ ወዘተረፈ… ሁሉ የሚገኙት በብዙ ድካም ነው። እናንተም ብዙ ፈተና እና ድካም አልፋችሁ ለዚህ ስለደረሳችሁ በድጋሜ እንኳን ደስ አላችሁ። ጥበብን ፍለጋ የሕይወት-ዘመን ጉዞ ነው። በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በቆያችሁባቸው ጊዚያት ያገኛችሁት ዕውቀትና ክህሎት ለጊዜው ራሳችሁን ለማኖር በሚያችል የሥራ መስክ ተሰማርታችሁ የምታገለግሉበት ብቻ መስሎ ሊታያችሁ ይችላል። የዕውቀት ዋና ዐምዱ “መንቃት” ስለሆነና በዕወቀት የነቃ አእምሮ ደግሞ ሥራ በተፈጠረበትና ተቀጥረው በሚሠሩበት ብቻ ሳይሆን ራሱን ሥራን እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ያስባል። ስለሆነም የሕይወት ትግሉ ከዚህ ከምረቃ ጊዜአችሁም በኋላ ቢሆን ይቀጥላል። ምናልባትም በተማራችሁበት የሙያ ዘርፍ መሠማራት የማትችሉበት ሁኔታ ቢፈጠርም እንኳ ለጥገኝነት እና ለድህነት ማንም እጁን እንደማይሰጥ እና ሥራ-አጥ ሆኖ እንደማይቀመጥ ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም ይህ ትውልድ በብዙ ፈተና የተፈተነ በመሆኑና በኢኮኖሚ ጠንካራ ለመሆን ራስን ስለመቻል ማንም ሊነግረው የማያስፈልገው ትውልድ መስሎ ይሰማኛል።

በድጋሜ እንኳን ደስ አላችሁ!!
መልካሙን ሁሉ ከልብ እመኝላችኋለሁ!!!

# የኃላፊዎች መልዕክት!



ዘውዱ እምሩ ጀምበሬ (ዶ/ር)
የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጅክ
ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት

የ2014 ዓ.ም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ተማሪዎች፣ የተመራቂ ቤተሰቦች፣ መምህራንና ሰራተኞች እንኳን ደስ አላችሁ!

ውድ ተመራቂዎች፡ ከሁሉ አስቀድሜ የዓመታት የድካማችሁን ውጤት ለምታዩበት ለዚህ የምረቃ ቀን በመብቃታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ!
በዩኒቨርሲቲያችን በተለያዩ ዘርፎች ስትከታተሉት የነበረው የዓመታት ትምህርትና ስልጠና ቆይታችሁ በምረቃችሁ ይጠናቀቅ እንጅ የሌላ ታላቅና ከዚህም በላይ በሕይወት ተሞክሮ፣ በተጨባጭ ልምምዶችና በሙከራዎች ይበልጥ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከታችሁን ወደምታዳብሩበት ትምህርት ቤት (የስራ ዓለም) የመግቢያ በራችሁ በመሆኑ ጉዞአችሁ ተጀመረ እንጂ አላለቀም፡፡

ይህም የሚሆነው እውቀትና ክህሎት በአንዱ መሠረት ላይ ሌላኛው እየተገነባ ሳያቋርጥ የሚያድግ ጨርሻለሁ በቃኝ ተብሎ የሚተው ንብረት ባለመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ሠፊ የመማሪያ መደረክ (የስራው ዓላማ) ደግሞ በዩኒቨርሲቲ ቆይታችሁ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የቀሰማችሁትን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በተግባር የምትፈተኑበት በውጤቱም ማንነታችሁን ሙሉ የምታደርጉበትና በፈጠራችሁበት አቅምም ያስተማራችሁንና ለዚህ ህልማችሁ መሳካት ጉልበት ለሆኗችሁ መምህራን፣ ወላጆቻችሁና ከሁሉም በላይ ለአገራችሁ እድገት አስተዋጽኦ በማበርከት ውለታ የምትከፍሉበት ጊዜ ነው፡፡

ወቅት ደግሞ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ አገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ያሉትን የእድገት ፍላጎቶችና በተጨባጭ ያሉትን ፈታች ሁኔታዎች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እየፈተሸ (እየተመራመረ) መፍትሔ የሚያመጣ የተማረ የሰው ሃይል ይበልጥ የምትፈልግበት ወቅት በመሆኑ ለዚህ ጥሪ እንደሃገር የበኩላችሁን አስተዋጽኦ ልታደርጉ በምትችሉበት አቅም ላይ በመድረሳችሁ ልትኮሩ ይገባችኋል፡፡

ይህንን አገሪቱ የምትፈልገውንና በምንም የማይተካ አስተዋጽኦ ለማበርከት ደግሞ በትምህርት በቆያችሁባቸው ዓመታት ከጨበጣችሁት እውቀትና ክህሎት በላይ በከፍተኛ ኃላፊነትና አገራዊ ፍቅር ለማገልገል መቁረጥ እጅግ ወሳኝ በመሆኑ ይህንን ኃላፊነት ትወጣላችሁ የሚል ከፍተኛ እምነቴን እየገለጽኩና በየተሰማራችሁበት የስራ መስክ ሁሉ ለትውልድ የሚተርፍ ውጤታማ ሥራ የምትሰሩበት ዘመን እንዲሆንላችሁ እየተመኘሁ በድጋሜ ለእናንተም ሆነ ለወላጆቻችሁ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡፡



Birilew Belayneh Tsegaw (PhD)
Director, Registrar Alumni and Management Directorate

On behalf of Registrar and Alumni Management Directorate, I am pleased to congratulate you for the successful accomplishing your study at Bahir Dar University.
Your graduation is such a great day to celebrate as you have successfully overcome the phase of studying hard after goes through different challenges — COVID - 19 Pandemic as well as unusual environment due to the security problems in the northern part of the country. A new phase of life starts right after graduation. Today is a new turning point in your life, beginning a path paved with more chances and opportunities.
I hope that you all will make us proud in your future career by providing an excellent professional service with honesty and dedication for your beloved country. Always remember that you are here in this world for a brief moment and do not miss the chance you have to leave a long lasting foot-print. Such a thought on daily basis will guard you from the temptations of unhealthy motives like selfishness, dishonesty and demotivation.
Lastly, I am wishing the best for all graduates to contribute significantly for the successful achievement of shared vision of our country at large and successful life and career.

# የስኬታማ ተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ

## ‹‹ዩኒቨርስቲ ማለት ላወቀበትና ለተጠቀመበት በሁለት ሰይፍ ተስሎ የሚወጣበት ነዉ፡፡››

ተማሪ እየሩሳሌም መስፍን



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመሬት አስተዳደር ተቋም በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከተቋሙ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነችው የመሬት አስተዳደር ትምህርት ክፍል ተማሪ በእንግድነት ይዘን ቀርበናል፡፡ ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ፣ ስለአሳለፈችው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ-ምልልስ አድርጋላታለች፡፡
መልካም ቆይታ!!

ዓባይ፡- በቅድሚያ ለቃለ ምልልስ ፈቃደኛ ስለሆንሽልን እያመሰገንን ራስሽ ለዓባይ አንባብያን ብታስተዋውቂልን?

እየሩሳሌም መስፍን እባላለሁ፡፡ የትዉልድ ቦታየ ደቡብ ጎንደር ጋይንት ዙሪያ ነው፡፡

ዓባይ ፡- የልጅነት አስተዳደግሽ የትምህርት ቤት ህይወትሽ ምን ይመስላል?

እየሩሳሌም፡- ያደግሁት አዲስ አበባ ልዩ ስሙ ገርጂ በሚባል አካባቢ ነዉ፡፡ ወደ አዲስ አበባ የሄዱሁበት ምክንያት ኑሮዉን አዲስ አበባ ያደረገ የእናቴ ወንድም ወደ አዲስ አበባ እናቴ እንድትመጣ ይፈልግ ነበርና እናቴ ደግሞ ልጄን ይዤ እሄዳለሁ ብላ ወሰደቺኝ፡፡ ከዛ ጀምሮ ኑሮየ አዲስ አበባ ሆነ፡፡ መጀመሪያ አዲስ አበባ እንደገባሁ መኖር የጀመርኩት ከአጎቴና ከአክስቴ ጋር ነበር፡፡ በወቅቱ ሁለቱም ስላላገቡ የሚኖሩትም አንድ ላይ ነበር፡፡ አጎቴ ሚስት ሲያገባ ሦስተኛ ክፍል እስከምሆን ድረስ ከእርሱ ጋር ቆየሁ፡፡ በወቅቱ እናቴ ሰዉ ቤት ተቀጥራ ትሰራ ነበርና ባጋጣሚ ከምትሰራበት ወጥታ ለትንሽ ቀናት ከኛ ጋር ተቀምጣ ነበር፡፡ ከዚያም ቤት እንድትከራይና እኔንም እንድትወስደኝ ተነገራትና ተከራይተን ወጣን፡፡ ከእናቴ ጋር የተወሰኑ ወራትን አብረን እንደኖርን የእናቴ አባት ለህክምና ወደ አዲስ አበባ መጥተዉ እዛዉ ቤት ክርስቲያን ያገለግሉ ጀመር፡፡ በዚያው አጋጣሚ አያቴ የሚያዉቋቸዉ አንዲት እናት እያስተማርኩ የማሳድጋት ልጅ ፈልጉልኝ ይሏቸዋል፡፡ አያቴም እኔን ወስደዉ አስረከቧቸዉ፡፡ ይህም የሆነዉ ሶስተኛ ክፍል ልጨርስ ስል(ግንቦት አንድ) ላይ ነበር፡፡ በዚያ ቤት አስረኛ ክፍል እስክደርስ ቆየሁ፡፡ ከአስረኛ ክፍል ግማሽ ሴሚስተር ጀምሮ ትምህርቴን እስከአጠናቅቅ እና አሁንም ከእናቴ ጋር እየኖርሁ ነው፡፡ እናቴ የቀለም ትምህርት የላትም፡፡ የምንተዳደረዉም አትክልት በመሸጥ በምታገኘዉ ገቢ ነዉ፡፡ እናቴ በአገኘቿዉ ነገር ተመስገን ብላ ደስተኛና ቀለል ያለ ሕይወት የምታኖር ነች፡፡ በዚህም ደስተኛ ነኝ፡፡ የትምህርት ሁኔታ ከአንደኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል በቦሌ ገርጂ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ፣ ከ9 እና 10 ለም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲሁም 11 እና 12 ቦሌ pre-paratory school ተምሬያለሁ፡፡ ዩኒቨርስቲ ደግሞ ፈጣሪ በፈቀደዉ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ደርሶኝ ከዚያም በመሬት አስተዳደርና ቅየሳ ትምህርቴን ተከታትያለሁ፡፡

ዓባይ ፡- ዩኒቨርስቲን እንዴት ትገልጪዋለሽ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ ምን ተማርሽበት?

እየሩሳሌም፡- ዩኒቨርስቲ ማለት ላወቀበትና ለተጠቀመበት በሁለት ሰይፍ ተስሎ የሚወጣበት ነዉ፡፡ ማለትም አንድ ተማሪ በአግባቡ ተምሮ፣ አንብቦ፣ እንዲሁም የተለያዩ ጫናዎችንና ግፊቶችን ተቋቁሞ አልፎ የመጣበትን አላማ ሳይዘነጋ በአለማዊዉ ትምህርቱ ዉጤታማ የሚሆንበትና ለቀጣይ ህይወቱ ታጥቆ የሚወጣበት ተቋም ነዉ፡፡ በተጨማሪም በፊት ካሣለፍነዉ የትምህርተ መርሃ ግብር ላቅ ባለ መልኩ የተማሪዎችን ጥረትና የጊዜ አጠቃቀም የሚጠይቅ ፣ማህበራዊ የአኗኗር ዘዴ የሚያለማምድና በእዉቀትና በክህሎት ብቁ ዜጎችን ማፍራት የሚችል ተቋም ነዉ፡፡ እንዲሁም ከአለማዊ ትምህርት ጎን ለጎን በመንፈሳዊ ሕይወትም የተሻለ መንገድ ለመያዝ ምክንያት ይሆናል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የመጡበትን አላማ ወደ ጎን በመተዉ አልባሌ ቦታ የሚወድቁበት ወይም የሚጠፉበት ሲሆን ይታያል፡፡

ዓባይ ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ፡፡ ባንቺ በኩል እንዴት አገኘሽው?

እየሩሳሌም፡- ይህን ሀሳብ እኔም እጋራዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዉ እዉቀት ለመጨበጥ ሳይሆን ፈተና ለማለፍ የሚያነብበት ሁሉም ማለት ባይቻልም መምህሮችም ትምህርቱን ለመሸፈን እንጂ ተማሪዉን እዉቀት ለማስያዝ የማይጥሩበት ሆኖ ይስተዋላል፡፡ በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ በሚያጋጥሙ ጉዳዮች ተከትሎ በመማር ማስተማሩ ላይ ተፅእኖ በማሳደሩና በአንድ ሲሚስተር የምንማረዉን በ45 ወይም 60 ቀናት ወስጥ ለመሸፈን በመደረጉ የትምህርት ለዛዉን የቀነሰዉ ይመስለኛል፡፡

ዓባይ ፡- የመምህራን እና የማስተማር ብቃት እንዴት ታይዋለሽ? ላንቺ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትይው አስተማሪ አለ? እንዴት?

እየሩሳሌም፡- በእዉነቱ የመምህራን የማስተማር ብቃት በመማር ማስተማሩ ላይ ትልቅ ቦታ አለዉ፡፡ መምህራን ያላቸዉን እዉቀት በአግባቡና ተማሪዉ በሚረዳዉ መልኩ ማስተላለፍ የሚችሉትና የተለያዩ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎቶች ማስተናገድ የሚችሉት መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት የይዘትና የተለያዩ የማስተማር አቀራረብ የተሟላ ዕውቀት ሲኖራቸዉ ነዉ፡፡ የትምህርት ጥራት እንዲኖር መምህራን በተለይ በማስተማር ስልትና ክህሎት ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ ብቁ መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድ የተለያዩ ምንጮችን በመጠቀም የማስተማር ሂደቱን ይገመግማሉ፣ የተማሪዎቻቸውን የእውቀትና የግንዛቤ ደረጃ ለመተንተንና ለመደገፍ ግብረ መልሶችንና የምዘና ውጤቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ይህም በተማሪዎች የትምህርት ውጤት ላይ የሚያሳድረው የተነሳሽነት መንፈስ ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ በእኔ ዉጤት ላይ ቦታ አላቸዉ የምላቸዉ መምህራን አሉ፡፡ ተማሪ ዉጤታማ የሚሆነዉ ከራሱ ጥረት በተጨማሪ ተገቢዉን ትምህርት ከመምህሩ ሲያገኝ ነዉ፡፡

ዓባይ ፡- በዩኒቨርሲቲው ቆይታሽ ውጤታማ ለመሆን የምትከተይው የአጠናን ስልትሽ ምን ይመስላል?

እየሩሳሌም፡- የምከተለዉ የጥናት ስልት የለኝም፡፡ ማንበብ ባለብኝ ሰዓት ደስ ያለኝን ኮርስ አነባለሁ፡፡ ብዙ የማነበዉም የሚሰጠን reading material ነዉ፡፡ አልፎ አልፎም አጋዥ መጽሐፍትን እጠቀማለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ከምሽቱ 2:00 -4:00 የማነብበት ጊዜ ነዉ፡፡

ዓባይ፡- በህይወትሽ እንደ አርዓያ የምትከተይው ማን ነው? ለምን?

እየሩሳሌም፡- ብዙ ግዜ ከብዙ ሰዎች ጠንካራ ጎናቸዉን እወስዳለሁ፡፡ ነገር ግን በሕይወቴ ዉስጥ እናቴ አርዓያየ ነች፡፡ ምክንያቱም እናቴ ማለት ነገሮችን በመልካም ነገር የምትተረጉም፣ ቢከፋት የማታማርር በጠቅላላዉ ለፈተና እጅ የማትሰጥ፣ ቀለል ያለ ሕይወት የምትኖርና ለወደፊቱ መልካምን ነገር ተስፋ የምታረግ እናት ነች፡፡

ዓባይ፡- እስካሁን ያለሽ አማካይ ውጤት ስንት ነጥብ ነው?

እየሩሳሌም፡- 3.85

ዓባይ ፡- ለውጤትሽ ከፍተኛ መሆን ምስጢሩ ምንድን ነው?

እየሩሳሌም፡- የተለየ ምስጢር የለውም፡፡ ያዉ በተቻለኝ መጠን የመጣሁበትን አላማ ለማሳካት መጣርና ይህም እንዲሳካ ፈጣሪን በፀሎት በመጠየቅ ነዉ፡፡

ዓባይ ፡- ድጋፍ የሚያደርግልሽ ማን ነው? የገንዘብ እጥረትስ አጋጥሞሽ ያውቃል ወይ?

እየሩሳሌም፡- የምትርዳኝ እናቴ ነች፡፡ በተጨማሪም ወደ ቤት በተመለስኩ ጊዜ ስራ ፈልጌ በመግባት የሚያስፈልገኝን ነገር አሟላለሁ፡፡

ዓባይ ፡- የእየሩሳሌም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ማህበራዊ ህይወቷ ምን ይመስላል?

ወደ ገጽ 7 የዞረ

# የስኬታማ ተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ

ከገጽ 6 የዞረ

እየሩሳሌም፡- ማህበራዊ ሕይወቴ ላይ ደከም ያልሁ ነኝ፡፡ ከጓደኞቼና ራሳቸዉ ቀርበዉ ከሚግባቡኝ ሰዎች በስተቀር ከሰዉ ጋር መግባባት አይሆንልኝም፡፡ ይህንንም መቀየር ያልቻልኩትና እንደ ትልቅ ድክመቴ የምወስደዉ ነዉ፡፡

ዓባይ ፡- በህይወትሽ የገጠመሽ ፈተና ነበር? ካለ እንዴት አለፍሽው?

እየሩሳሌም፡- ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁንና በሕይወቴ ዉስጥ ከባድ ነዉ የምለዉ ችግር ገጥሞኝ አያዉቅም ነገር ግን ትንሽ በኢኮኖሚ ዝቅ ያልን ስለሆንን በትንሹም ቢሆን ለእኔ ፈተና ነዉ፡፡

ዓባይ ፡- ወደፊት ለኢትዮጵያ ምን ትመኛለሽ?

እየሩሳሌም፡- ለሀገሬ የምመኝላት ፈጣሪ በምህረት አይኖቹ ተመልክቶንና ይቅር ብሎን ይህ የዘረኝነት መንፈስ ጠፍቶ በሀገራችን ላይ አባቶቻችን ያስተላለፉልንን ሰላም፣ ፍቅርና መቻቻል የሚሰፍንባት እንዲሁም በእድገት ጎዳና የምትጓዝ ሀገር እንድትሆን እመኛለሁ፡፡

ዓባይ ፡- ማመስገን የምትፈልጊው አካል ካለ?

እየሩሳሌም፡- መጀመሪያ አመሰግነዉ ዘንድ ምክንያቴ ብዙ ነዉና በህይወቴ ዘመን ሁሉ ሳልተለየኝ ለልዑል እግዚአብሔርና ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናየን አቀረባለሁ፡፡ በመቀጠል ለሕይወቴ ብርሀን ለሆነችሁ እናቴ እንዲሁም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሕይወቴ ጉዞ ላይ አሻራችሁን ያሳረፋችሁን በሙሉ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡
ዓባይ፡-ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡
እየሩሳሌም፡- እኔም አመሰግናለሁ ፈጣሪ ያክብርልኝ፡፡

ከገጽ 11 የዞረ

ዓባይ፡- ዩኒቨርሲቲ የመግባት ዕድሉን ባታገኝ በምን የስራ ዘርፍ የምሰማራ ይመስልሃል?

ሞገስ፡- ዩኒቨርሲቲ የመግባት እድሉን ባላገኝ የልጅነት ህልሜ ስለነበር መከላከያ ሰራዊት እሆን ነበር፤ አሁንም ሙያውን እወደዋለሁ፡፡

ዓባይ፡- በህይወትህ የገጠመህ ፈተና ነበር? ካለ እንዴት አለፍከው?

ሞገስ፡- ይኽ ነው የምለው ከባድ ፈተና ገጥሞኝ አያውቅም፡፡

ዓባይ፡- የወደፊት ራዕይህን እንዲሁም ለኢትዮጵያ ምን እንደምትመኝላት ብትነግረን?


ሞገስ፡- የወደፊት ህልሜ ኀበዝ ኢንተርናሽናል የእግር ኳስ ዳኛ መሆን ነው፡፡ ለኢትዮጵያ የምመኝላት ሰላም እድገትና ብልፅግና ነው፡፡

ዓባይ፡- የምትጨምረው ሀሳብ ካለና ማመስገን የምትፈልገው አካል ካለ ብትነግረን?

ሞገስ፡- ማመስገን የምፈልጋቸው ብዙ ሰዎች አሉ፤በቅድሚያ ግን ከዚህ ላደረሰኝ ሀያሉ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው እያልኩ በጣም ኀበዙ አባቴ፣እናቴ እህትና ወንድሞቸ፣ የትልቅ እህቴ ባለቤት አቶ ጀጀው ታዬ እንዲሁም አስተማሪዎቼ ሁሉንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ዓባይ፡- ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

ሞገስ፡- እናንተም ስለጋበዛችሁኝ እግዚአብሄር ይስጥልኝ አመሰግናለሁ::




ከገጽ 15 የዞረ

ዓባይ፡-የህይወትህ አርዓያ ማን ነው? ለምን?

ሰለሞን፡- የእኔ አርያዬ አላማዬ ነው፡፡ ይህ ሲባል ከራስ ወዳድነት የመነጨ ሊመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን ቅድም ከላይ እንደጠቀስኩት ያደኩበት ማህበረሰብ ለትምህርት ያለው እይታ በጣም የወረደ በመሆኑ፣ አባቴም የዚያ ማህበረሰብ አባል እንደመሆኑ ሰው ተምሮ እሚለወጥ አይመስለውም፡፡ በጣም ብዙ ጓደኞቼ የዓሳ እራት ሆነው የቀሩ አሉ፡፡

በአጭሩ ሃብታም ለመሆን በሚል አጉል አስተሳሰብ፡፡ ነገር ግን ይሄ ሁሉ ፈተና አልፌ ከቤታችን እኔ ብቻ ነኝ እስከዚህ እየታገልኩ የደረስኩት፡፡ ወደዚህ እንድደርስ ያደረገኝም ከህጻንነቴ ጀምሮ ያስቀመጥኩት ራዕይ ነበረኝ፡፡ ያ ራዕይ ለወላጆቼ ሆኜ ማሳይት የምፈልገው ነገር ነው፡፡ ያ ህልም እንግዲህ በእግዚያብሔር ፈቃድና በእኔም ጥረት እየተፈጸመ ይመስለኛል፡፡

ዓባይ፡- እስካሁን ያለህን አማካይ ውጤት ስንት ነጥብ ነው?
ሰለሞን፡- እስካሁን ያለኝ አማካኝ ውጤት 3.77 ነው፡፡
ዓባይ፡- ለስኬትህ ምስጢሩ ምንድን ነው?

ሰለሞን፡- የስኬቴ ሚስጢር በአጭሩ አንደኛ የፈጣሪ ፈቃድ፣ ሁለተኛ የእኔ ብርታት እና የጓደኞቼ እንዲሁም የእህቴ እገዛ ሶስተኛ የወላጆቼ እገዛ አለመኖር ምክንያቱም እንድጠነክር ስላደረገኝ ነው እነዚህ ናቸው፡፡

እርዳታ ባታደርግልኝም የሞራል ድጋፏ አግዞኛልና ሳላመሰግን አላልፍም፡፡ ሌላው የገንዘብ ችግር ነበረብኝ ግን እንደ ችግር አላየውም፡፡ አንዳንዱ ገንዘቡ ወደ አልተፈለገ ቦታ ሲወስደው ሳይ ለበጎ ነው ብዬ እራሴን አጽናናለሁ፡፡

ዓባይ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወትህ ምን ይመስላል?

ሰለሞን፡- በበለጠ ከላይ ገልጨዋለሁ፡፡ ከክላስ ጓደኞቼ፣ ከዶርም ልጆች እንዲሁም ከመምህራኖቼ ጋር ጥሩ መግባባት አለብኝ፡፡ የግቢ ማህበራዊ ህይወቱም በጣም ደስ ይላል ጥሩ ነው፡፡

ዓባይ፡- በህይወትህ የገጠመህ ፈተና ነበር? ካለ እንዴት አለፍከው?

ሰለሞን፡- በሕይዎት ዘመኔ ከባድ የሚባል ነገር ብዙም አልገጠመኝም፡፡ ነገር ግን እንደሚታወቀው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ትንሽ ይፈትናል፡፡ ወላጆቼን በአካል ማግኘት አልቻልኩም፡፡ በስልክ ነው እስካሁን እያገኘዋቸው ያለሁኝ፡፡ እንዴት አለፍከው ለሚለው ችግሩ የሀገር ችግር እንጂ በእኔ ብቻ የደረሰ ችግር ባለመሆኑ በመረዳት ራሴንም በማጽናናት እያለፍኩት ነው፡፡

ዓባይ፡- ወደፊት ለሃገርህ ምን ትመኛለህ?

ሰለሞን፡- ወደ ፊት ለኢትዮጵያ የምመኘው ቢኖር በተማርኩበት ሙያ ሳልሰለችና ሳልሰስት ማገልገል ነው፡፡ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ተማሪ ለማነጽ ለገንዘብ ሳይሆን ለእውቀት ብሎ የሚማር ተማሪ ለመፍጠር እንዲሁም ኢትዮጵያ ወደ ነበረችበት የስልጣኔ ማማ ለመመለስ በተቻለኝ መጠን እጥራለሁ፡፡ ለአስተማሪነት ጥሩ ዜጋ ለማምረት ቁልፉ ስራ ስለሆነ፡፡

ዓባይ :-ማመስገን የምትፈልገው አካል ካለ እድሉን ልስጥህ?

ሰለሞን፡- ከሁሉም አስቀድሞ ሁሉም በእርሱ ለሆነውና ለሚሆነው ለፈጠሪ በመቀጠል ለወላጆቼ፣ ለእህት ለወንድሞቼ፣ ለመምህራኖቼ፣ ለክላስ ጓደኞቼ፣ ለሀገሬም እንዲሁም ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመጨረሻም ይህንን ሀሳቤን እንድገልጽ ዕድሉን ለሰጠኝ ለአባይ ጋዜጣ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ዓባይ፡-ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

ሰለሞን፡- እኔም ይህንን ዕድል በመስጠት የዓባይ ጋዜጣ እንግዳችሁ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ! እግዚያብሔር ይስጥልኝ!

# ‹‹…ሳይማሩ እኔን አስተምረው መክረው እዚህ ያደረሱኝ ቤተሰቦችና የመረቁኝ ሽማግሌዎች ውጤት እኔን ስኬታማ አድርጎኛል›› ተማሪ ብርሃኑ ቤዮሮ



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ ወር 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂውማኒቲስ ፋካሊቲ በ2014 ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከፋካሊቲው ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነው የእንግሊዘኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪን በእንግድነት ይዘን ቀርበናል፡፡

ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታው፣ ስለአሳለፈው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ-ምልልስ አድርጋለች፡፡ መልካም ቆይታ!!

ዓባይ፡-በቅድሚያ ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆንህ በዝግጅት ክፍላችን ስም እያመሰገንን የላቀ ውጤት በማስመዝገብህ እንኳን ደስ አለህ፡፡ እስቲ እራስህን ለዓባይ አንባብያን አስተዋውቅልን?

ስሜ ብርሃኑ ቤዮሮ እባላለሁ፤ የትውልድ ቦታየም በደቡብ ክልል በሚገኘው ከምባታ ጠምባሮ ዞን በአንጋጫ ወረዳ በቀእለማ ቀበሌ ልዩ ስሙ በዳጃኒቾ በተሰኘ ስፍራ ነው፡፡

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግህ እና የትምህርት ቤት ህይወትህ ምን እንደሚመስል ብንጨዋወት?

ብርሃኑ፡- ምንም ካልተማሩ ቤተሰቦቼ ተውልጄ በአካባቢው ካሉ ሞዴል/ አርአያ የሚሆኑ ሰዎችን ፈለግ በመከተል ነገሮችን በሰከነ አስተሳሰብ በማየት እኔም ከሌሎች የተሻለ ሰው ለመሆን እና መልካም አርአያ በማሳየት ጠንካራ አቋም ይዤ አድጌአለሁ፡፡ በተጨማሪም ወላጆቼ እነሱ ባይማሩም እኔን በማስተማራቸው የበረከት ምንጮቼ እንደሆኑ በማሰብ ታዛዥ እና ታላላቆቼን በማክበር ከቤተሰቦቸ በዘለለ በአካባቢው የሚኖሩ አቅመ ደካሞችን ወይም ሽማግሌዎችን አቅሜ በፈቀደው ልክ በማገዝ ለነገ ስንቅ ይሆናል ብዬ ምረቃት እያገኘሁ አድጌአለሁ፤ ዛሬ ላይ ቆም ብዬ ሳስበው ለችግሮች መሸጋገሪያ ድልድዩ እንደሆነኝ አምናለሁ፡፡ የትምህርት ቤት ህይወቴም ከመምህራን እና ከተማሪዎች ጋር በመግባባት ጠንካራ ማህበራዊ ህይወት በመመስረትና ጓደኛ የውድቀትም ይሁን የስኬት መነሻ እንደሚሆን በማሰብ ጥሩ አስተሳሰብ ያላቸውን ውስን ጓደኛ በመምረጥ እና ገና ከልጅነቴ ጀምሬ አላማየን የማሳካት ራዕይ ይዤ ሁሉንም ሰው በእኩል አይን በማየት ህይወቴን አስቀጥያለሁ፡፡

ዓባይ፡- የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ህይወት እንዴት ትገልፀዋለህ? በዩኒቨርሲቲ ቆይታህ ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ ምን ተማርህ?

ብርሃኑ፡- ዩኒቨርስቲ የእውቀትና የክህሎት ምንጭ ሲሆን ትውልድ የሚቀረፅበት፣ ለሌሎች ተቋማት መሰረት የሚጣልበት ቦታ ነው፡ ፡ እኔም በቆይታየ የተለያዩ ቋንቋዎችን፣ ባህሎችንና መልካም ተሞክሮዎችን የተላመድኩበት ነው፡፡

ዓባይ፡- የምን ትምህርት ክፍል ተማሪ እንደሆንክ እና እስካሁን ያለህ አማካኝ ውጤት ስንት እንደሆነ ብትገልፅልን?

ብርሃኑ፡- የእንግሊዘኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪ ስሆን እስካሁን ያለው አጠቃላይ ውጤቴ 3.63 ነው፡፡

ዓባይ፡- የመምህራንን የማስተማር ብቃት እንዴት ታየዋለህ? ላንተ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትለው አስተማሪ ካለ ብታስተዋውቀን?

ብርሃኑ፡- ሁሉም መምህራን ብቁ ሁሉም ደግሞ ደካማ ብሎ ለመፈረጅ ይከብዳል፤ ምክንያቱም አንዳንዶቹ የዩኒቨርሲቲውን ዓላማ ለማሳካትና የነገ አገር ተረካቢ ብቁ ትውልድ ለማፍራት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በየዕለቱ ትክክለኛ ስራ የሚሰሩ አሉ፡፡ በዚያው ልክ "የሚያገኙትን ከማጣት" አይነት ስራ ሲያከናውኑና የሚያስተምሩት ትምህርትና የሚያሳዩት ተግባር የማይዛመድ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው የመልካም መምህራን ስም የሚያበላሹም አያታጡም፡፡

ዓባይ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ፤ በአንተ እይታ እንዴት ትገልፀዋለህ?

ብርሃኑ፡- እኔም በጣም እስማማለሁ፡ ፡ እኔ ዩኒቨርሲቲ ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይቸው አላውቅም፤ አንዳንዴ ሳስበው የዩኒቨርሲቲው ስርዓተ ትምህርቱ ፈተና ተኮር ሆኖ የተቀረፀ እስከሚመስል ድረስ እውቀት ተኮር ፈተና ለኔ ገጥሞኝ አያውቅም፤ ይህ አሰራር በተለምዶ የቀጠለ እንጂ የተማሪዎች ፍላጎትና የዩኒቨርሲቲው ዓላማ አይመስለኝም፡ ፡ ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ የተቀየረ ነገር እኔ የማላውቀው ሊኖር ይችላል ብዬ እገምታለሁ፡፡ በእኔ እምነት ትምህርት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እውቀት ተኮር ሳይሆን ፈተና ተኮር እንዲሆን ያደረጉት ምክንያቶች በኮረና ወረርሽኝ ምክንያት በትምህርት ላይ የተፈጠረው ተፅኖ፣ የሀገሪቱ ፀጥታ በየጊዜው መደፍረስ፣ ከፖለቲካና በየጊዜው የሚቀያየረው ስርዓተ ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት ያላማከለ መሆንና የመሳሰሉት ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

ዓባይ፡- በዩኒቨርስቲው ቆይታህ ውጤታማ ለመሆን የምትከተለው የአጠናን ስልትህ ምን ይመስላል?

ብርሃኑ፡- የምሰራቸውን ስራዎች ዝርዝር በማውጣት በቅደም ተከተል መቅደም የሚገባውን እያስቀደምኩ ጊዜዬን በአግባቡ መድቤ ያለ ምንም ቸልተኝነት ስራዬን በአግባቡ አጠናቅቃለሁ፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ራሴን ልክ እንደወታደር በመቁጠር ሁሌም ለመማር ዝግጁ በመሆንና መምህሩ በሚሰጠው ትምህርት ብቻ ሳልወሰን ከቤተ-መፅሐፍት እና ከኢንተርኔት የምፈልጋቸውን በማንበብ የእውቀት አድማሴን አሰፋለሁ፡፡ በተጨማሪም ከእኔ በእውቀት የተሻሉትን በመምረጥ የጎደለኝን ክፍተት እሞላለሁ፡፡

ዓባይ፡- በዩኒቨርሲቲ ቆይታህ ለስኬቱ ምክንያት የሆነኝ ምስጢሩ ምንድን ነው ትላለህ?

ብርሃኑ፡- የወደፊት ያለኝ ጠንካራና ፅኑ አቋሜ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል በቀን፣ በሌሊት፣ በብርድ፣ በሙቀት የምሰራቸውን ስራዎች በአግባቡ በማከናወኔ ስኬታማ ሆኛለሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ በተጨማሪም ሳይማሩ እኔን አስተምረው መክረው እዚህ ያደረሱኝ ቤተሰቦችና የመረቁኝ ሽማግሌዎች ውጤት እኔን ስኬታማ አድርጎኛል፡፡

ዓባይ፡- ለዚህ ደረጃ እንድትደርስ አርዓያህ ማን ነው? እንዴት?

ብርሃኑ፡- ለዚህ ደረጃ ያበቁኝ ቤተሰቦቸ ምንም እንኳ በቂ የገንዘብ ድጋፍ ባያደርጉልኝም ሳይማሩ ያስተማሩኝ፣ እነሱ ሳይበሉ እያበሉኝ፣ ሳይለብሱ እያለበሱ ለዛሬ ደረጃ እንድደርስ ድልድዩ ሆነውኛል፡፡ ሌላው በበጎ አድራጎታቸው የረዱኝ ሰዎችና ሳይሰስቱ እውቀታቸውን ለለገሱኝ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ለኔ ሞዴሌ በመሆናቸው ለዚህ እንድደርስ አድርገውኛል፡፡

ዓባይ፡-የግቢ ማህበራዊ ህይወትህ ምን ይመስላል?

ብርሃኑ፡- ከሱስና ከአልኮል ነክ ነገሮች ነፃ ሆኜ የዩኒቨርሲቲውን ህግና ደንብ በማክበር እንዲሁም ከሁሉም ማህበረሰብ ጋር በመከባበር ጥሩ የዩኒቨርሲቲ ህይወት አሳልፌአለሁ፡ ፡ ምንም እንኳ ከቤተሰቦቸ ብርቅም ዓላማየን ለማሳካት በየዕለቱ እውቀትን ለመሸመት ሁሌም በመጣር ላይ ጊዜዬን አሳልፋለሁ፡፡

ዓባይ፡- በሃሳብም ሆነ በገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግልህ ማን ነው? ከዚህ ጋር በተያያዘ ምን አጋጥሞህ ያውቅ ይሆን?

ብርሃኑ፡- በህይወቴ እጅግ በጣም ፈተና የሆነብኝ ነገር የገንዘብ እጥረት ነው፤ ገንዘብ ደግሞ የሁሉም ነገር አንቀሳቃሽ ነዳጅ ስለሆነ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ከትምህርቴ እንዳልስተጓጎል ያለኝን ጠንካራ አቋም ለማጎልበት የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለምሳሌ በበጋው ስማር እንዳልቸገር ስራ ክቡር ነው በሚል መንፈስ በክረምት ወቅት ወይም ትምህርት በማይኖረኝ ሰዓት የቀን ስራ እየሰራሁና ከበጎ ፈቃደኞች የማገኘውን ገንዘብ በመቆጠብ የነገን ተስፋ እያሰብኩ ስለምሰራ ለዚህ ደረጃ ደረስኩ፡፡

ዓባይ፡- በህይወትህ የገጠመህ ፈተና ካለ እና ከፈተናው ያለፍህበትን ዘዴ ብታጫውተን?

ብርሃኑ፡-- በህይወቴ ያጋጠሙኝ በርካታ ፈተናዎች ስለሆኑ ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ በኋላ ያጋጠሙኝን ፈተናዎች ለመጥቀስ ብሞክር ይሻለኛል፡፡ አንዱ የገንዘብ እጥረትሲሆን በዓለም አቀፍ የተከሰተው የኮረና ወረርሽኝ፣ በአገር ውስጥ የተከሰተው ጦርነት፣ የሃገሪቱ የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የሐይማኖት ችግሮች በቀጥታም


ሆነ በተዘዋዋሪ በትምህርቴ ላይ በተወሰነ መልኩ ችግር ሊጥሉብኝ ሞክረዋል፡፡ ከነዚህ ችግሮች በኋላ ትምህርት ስንጀምር የትምህርቱ መደራረብና የጊዜ እጥረት ቢያጋጥመኝም የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለምሳሌ የዛሬ ሀዘን የነገ ደስታ፣ የዛሬ ጨለማም የነገ ብርሃን ነው፣ ዛሬ ለራሴ ብኖር ነገ ደግሞ ለሌሎች እንደምኖር ፅኑ እምነት ይዤ፤ ሁሉም መልካም ነገር ከችግር በኋላ እንደሚገኝ በመገንዘብ ፈተናውን አልፌዋለሁ፡፡

ዓባይ፡- የወደፊት ራዕይህን እንዲሁም ለኢትዮጵያ ምን እንደምትመኝላት ብትነግረን?

ብርሃኑ፡- የወደፊት ምኞቴ የኢትዮጵያን አደራ ተቀብዬ ሀገሬ በእኔ ዘመን እንኳ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በዘርና በሐይማኖት ምክንያት የተጎዳችው መለወጥ አለባት የሚል ፅኑ አቋምና ተስፋ አለኝ፡፡ እንዲሁም ኢትዮጵያ የበለፀገችና ካደጉት አገር ቀድማ እንድትገኝ ምኞቴ ነው፡፡ የወደፊት ራዕዬም በተለያየ ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠርና ለሃገሪቱ የመዳን መንገድ እንደምሆን በውስጤ አምኛለሁ፡፡

ዓባይ፡- ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን

ብርሃኑ፡- እኔም ስለጋበዛችሁኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!




# የስኬታማ ተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ

<<ዩኒቨርሲቲ ማለት ትንሿ ኢትዮጵያ ማለት ነው፡፡ ካወቅህበት ብዙ ነገር ትማርበታለህ ካላወቅህበት ትጠፋበታለህ፡፡ ከቀለም ትምህርት ውጪ የተማርኩበት ነገር እንዴት ከማታውቀው ሠው ጋር አብረህ በሠላም መኖር እንደሚቻል ነው>>፡፡ እንዳለ ለማ



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከኮሌጁ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነው የሜዲስን ትምህርት ክፍል ተማሪ በእንግድነት ይዘን ቀርበናል፡፡

ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታው፣ ስለአሳለፈው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብቃለ-ምልልስ አድርጋለች፡፡ መልካምቆይታ!!
ለቃለ-ምልልስ ፈቃደኛ ስለሆኑ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

ዓባይ፡- በቅድሚያ ስምህን እና የትውልድ ቦታህን ብትገልጥልን?

ስሜ እንዳለ ለማ ይባላል የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 2014 እጩ ተመራቂ ነኝ የትዉልድ ቦታየ ሰሜን ሸዋ ዞን አሳግርት ወረዳ ከደብረ ብርሃን 70 ኪ.ሜ የሚርቅ ቦታ ነው፡፡

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግህ የትምህርት ቤት ህይወትህ ምን እንደሚመስል ብታብራራው?

እንዳለ፡- የተወለድሁት እና ያደግሁት ገጠር ነው፡፡ ቤተሠቦቼን በግብርና እያገዝኩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን አንድ ሠአት እየተጓዝሁ ተማርኩ፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ዶርም ተከራይቼ ስንቅ እያመላለስኩ ተማርኩ፡፡

ዓባይ፡- ዩኒቨርስቲን እንዴት ትገልጠዋለህ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርህበት ነገር ምንድን ነው?

እንዳለ፡- ዩኒቨርሲቲ ማለት ትንሿ ኢትዮጵያ ማለት ነው፡፡ ካወቅህበት ብዙ ነገር ትማርበታለህ ካላወቅህበትትጠፋበታለህ፡፡ ከቀለም ትምህርት ውጪ የተማርኩበት ነገር እንዴት ከማታውቀው ሠው ጋር አብረህ በሠላም መኖር እንደሚቻል ነው፡፡

ዓባይ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ፡ ፡ ባንተ በኩል እንዴት አገኘኸው?

እንዳለ፡- አንዳንድ ጊዜ እውነት ነው እውቀት ተኮር ቢሆን ጥሩ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ practice based ቢሆን እላለሁ፡፡

ዓባይ፡- የመምህራን እና የማስተማር ብቃት እንዴት ታየዋለህ? ላንተ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው ;የምትለው አስተማሪ አለ?

እንዳለ፡- ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉ መምህራን የማስተማር ብቃታቸው ጥሩ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን የባህሪ ችግር ያለባቸው አሉ፡፡ ለኔ ዉጤታማነት የሁሉም መምህራን አስተዋጾ አላቸው፡፡ ማለቴ ከአንደኛ ክፍል እስካሁን ያስተማሩኝ ሁሉ
አባይ፡- በዩኒቨርስቲው ቆይታህ ውጤታማ ለመሆን የምትከተለው የአጠናን ስልት ምን ይመስላል?
እንዳለ፡- ሰአቴን በአግባቡ እጠቀማለሁ፡፡ በተጨማሪም ሳነብ ሙሉ ትኩረቴን ሰጥቼ አነባለሁ፡፡

ዓባይ፡-በህይወትህ እንደ አራያ የምትከተለው ማን ነው?

እንዳለ፡- የተለየ እንደ አርአያ የምከተለው ሠው የለም፡፡

ዓባይ፡- እስካሁን ያለህ አማካይ ውጤት ስንት ነጥብ ነው?

እንዳለ፡- አማካይ ውጤቴ 3.77 ነው፡፡

ዓባይ፡-ለስኬትህ ምስጢሩ ምንድን ነው?

እንዳለ፡- ለስኬቴ ሚስጥሩ እግዚአብሔር እና ጠንክሮ መስራት ነው፡፡

ዓባይ፡- ድጋፍ የሚያደርግልህ ማን ነው? የገንዘብ እጥረትስ አጋጥሞህ ያውቃል ወይ?

እንዳለ፡-ድጋፍ የሚያደርጉልኝ ቤተሠቦቼ ናቸው፡፡ እናት እና አባቴ እንዲሁም ወንድም እና እህቶቼ ሁሉም፡፡ ከበድ ያለ የገንዘብ ችግር አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡

ዓባይ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወትህ ምን ይመስላል?

እንዳለ፡-የግቢ ማህበራዊ ህይወቴ በጣም ደስ ይል ነበር፡፡ ከተለያየ ቦታ የመጡ ጓደኞቼ ጋር በጣም ተግባብተን በመረዳዳት በፍቅር ነበር የቆየነው፡፡

ዓባይ፡-በህይወትህ የገጠመህ ፈተና ነበር ? ካለ እንዴት አለፍኸው?

እንዳለ፡- የገጠመኝ ፈተና 10ኛ ክፍል mathes የማትሪክ ውጤቴ ሲሠረዝብኝ፡፡ ከባድ ነበር ግን ከእግዚአብሔር እና ቤተሠቦቼ ጋር ታለፈ፡፡

ዓባይ፡-ወደፊት ለኢትዮጵያ ምን ትመኛለህ?

እንዳለ፡- ለኢትዮጵያ የምመኘው ሠላም ሠላም ሠላም ..........ነው፡፡

ዓባይ፡- ማመስገን የምትፈልገው አካል ካለ?

እንዳለ፡- ማመስገን የምፈልገው 1ኛ. እግዚአብሔርን ለዚህ ስኬት ስላበቃኝ፤2ኛ.ለቤተሠቦቼን፤3ኛ. ለጓደኞቼ፤4ኛ. ለመምህራኖቼ እና ለሁሉም ከጎኔ ለነበሩት በሙሉ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ዓባይ፡-ለነበረንቆይታእናመሰግናለን፡፡

እንዳለ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# የስኬታማ ተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ

## ‹‹ለዚህ የበቃሁት ክረምት አዲስ አበባ በመሄድ ሎተሪ በመሸጥ፣ በረሃ በመሄድ ስራ በመስራት ነው›› ተማሪ ቢንያም ፈንታሁን



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን ዓባይ በነሐሴ 2014 ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች በባዮሎጅ ትምህርት ክፍል ከኮሌጁ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነውን ተማሪ በእንግድነት ይዘን ቀርበናል።

ዓባይ፡- ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ እያመሰገንን በቅድሚያ ስምህን እና የትውልድ ቦታህን ብትገልጥልን?

---፡- ስሜ ተማሪ ቢንያም ፈንታሁን እባላለሁ። የተወለድሁት በምዕ/ጎጃም ዞን በደቡብ ሜጫ ወረዳ አብሮ መኖር ቀበሌ ልዩ ስፍራው ገንቦ ማርያም እየተባለ በሚጠራ ስፍራ ነው።

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግህ የትምህርት ቤት ህይወትህ ምን እንደሚመስል ብታብራራው?

ቢንያም፡- የልጅነት አስተዳደጌ ገጠር እንደመወለዴ መጠን ከብት እጠየጠበቅሁና የግብርና ስራን እየሰራሁ ካደግሁ በኋላ በአስር አመቴ ገንቦ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ገባሁ። በትምህርት ቤት ቆይታየም ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ደረጃ ለቅቄ አላውቅም።

ዓባይ፡- የዩኒቨርስቲን ህይወት እንዴት ትገልጸዋለሁ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርህበት ነገር ምንድን ነው?

ቢንያም፡- ዩኒቨርሲቲ ማለት ህብረ-ብሄራዊነት ማለትም የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ አነጋገሮች ወዘተ ያለበትና የሁሉም ብሄር እኩልነት ጠብቆ እውቀትን የሚያጎናጽፍ ተቋም ነው። ከዩኒቨርሲቲ ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርሁት ነገር ቢኖር ህብረተሰባዊነት፣ የሀሳብ መጋራት፣ ወንድማማችነት፣ መቻቻልና የተለያዩ አለመግባባቶችም ቢኖሩም በውይይት መፍታትን ተምሬበታለሁ።

ዓባይ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ። ባንተ በኩል እንዴት አገኘሽው?

ቢንያም፡- ዩኒቨርሲቲ ማለት ለእኔ የወደፊት ህይወት እንዴት መምሰል እንዳለባት መንገዱን የሚያሳይና የተማሪዎችን እውቀት የሚያበለጽግ ተቋም ነው እንጂ ፈተና ተኮር አይደለም።

ዓባይ፡- የመምህራን እና የማስተማር ብቃት እንዴት ታየዋለህ? ላንተ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትለው አስተማሪ አለ? እንዴት?

ቢንያም፡- የመምህራን የማስተማር ብቃት ጥሩ ነው። ነገር ግን ብዙ ብቃት የሌላቸው መምህራን አሉ። አንድ ሰው ብቃት ከሌለው ሰው ተምሮ እንዴት ብቃት /ውጤታማ/ ይሆናል። ለእኔ ውጤታማነት ልዩ ቦታ ያለው አስተማሪ ዶ/ር ደስታው ዳምጤ ነው፡ ፡ ምክንያቱም 1ኛ አመት እያለሁ እሱ የዲፓርትመንት መሪ ነበርና በዚያን አመት እኔ የዲፓርትመንቱ ሰቃይ ነበርሁ እናም የምስክር ወረቀት ሰጥቶኛል። ይህም እኔን በደንብ እንዳነብ አበረታትቶኝ ለዚህ ውጤት አብቅቶኛል።

ዓባይ፡- በዩኒቨርስቲው ቆይታህ ውጤታማ ለመሆን የምትከተለው የአጠናን ስልትህ ምን ይመስላል?

ቢንያም፡- የአጠናን ስልቴ፣ ጊዜና ገንዘብን በአግባቡ ነው የምጠቀመው። ለሁሉም ተግባሮቼ የጊዜ ሰሌዳ አላቸው። ለምሳሌ የምዝናናበት፣ ወደቤተ-ክርስቲያን የምሄድበትና ከጓደኞቼ ጋር የምንረዳዳበት ከሁሉም በላይ ግን ለእኔ ጥሩ ውጤት ማምጣት ምስጢሩ ዛሬ የተማርኩት ዛሬ ጠንክሬ ማጥናቴና መከለሴ ነው።

ዓባይ፡- በህይወትህ እንደ አርዓያ የምትከተለው ማን ነው? ለምን?

ቢንያም፡- በአርአያነት የምከተለው ተማሪ ዮሴፍ አለምነህ ነው። ምክንያቱም እሱ የጊዜ አጠቃቀምና የንባብ ስልትን በአግባቡ ስላስረዳኝና ተጠቅሜበትም ውጤታማ ስለሆንሁ።

ዓባይ፡- እስካሁን ያለህ አማካይ ውጤት ስንት ነው?

ቢንያም፡- 3.93

ዓባይ፡- ለስኬትህ ምስጢሩ ምንድን ነው?

ቢንያም፡- ለስኬቴ ምርጢሩ ጠንክሬ ማጥናቴና ያቀድሁት ራዕይ ስላለ ነው። ይህም ራዕይ እስካሁን ባለው ውጤት ተሳክቷል። ለወደፊቱም እግዚአግሔር ያውቃል።

ዓባይ፡- በገንዘብም ይሁን በሃሳብ ድጋፍ እና እገዛ የሚደረግልህ ከማን ነው? በዚህ በኩል ምን አጋጥሞአችሁ ያውቃል? ብታጫውተን?

ቢንያም፡- ማንም የደገፈኝ የለም፡ ፡ የምማረው ክረምት አዲስ አበባ በመሄድ ሎተሪ በመሸጥ፣ በረሃ በመሄድ ስራ በመስራት ገንዘብ በመፈለግ ነው የተማርሁት፡ ፡ይህም ሆኖ ግን ለስኬት በመብቃቴ በጣም ተደስቻለሁ፡ ፡ የገንዘብ እጥረትም ከአንድ ሁለት ጊዜ ገጥሞኝ ነበር። ነገር ግን አሸንፌው ለዚህ በቅቻለሁ።

ዓባይ፡- በዩኒቨርሲቲ ቆይታህ ማህበራዊ ህይወትህ ምን ይመስላል?

ቢንያም፡- የግቢ ህይወቴ በጣም ጥሩ ነበር የማጠናውና የምረዳዳው ከጓደኞቼ ጋር ነበር። እናም በግቢ ውስጥ ጥሩ ህይወትን አሳልፊያለሁ።

ዓባይ፡- በህይወትህ የገጠመህ ፈተና ነበር? ካለ እንዴት አለፍኸው?

ቢንያም፡- አዎ! የገጠመኝ ፈተና 12ኛ ክፍል ለመፈተን አንድ ወር ሲቀረኝ የገንዘብ እጥረት አጋጥሞኝ ነበር እናም ንባብ አቋርጬ የቀን ስራ በመስራት ለማለፍ ችያለሁ።

ዓባይ፡- ወደፊት ለኢትዮጵያ ምን ትመኝላታለህ?

ቢንያም፡- ለወደፊት ለኢትዮጵያ ሠላምን፣ እድገትን፣ በጋራ መስራትን፣ መከባበርን፣ ቁርጠኝነትን እመኛለሁ።

ዓባይ፡- ማመስገን የምትፈልገው አካል ካለ እድሉን ተጠቀም?

ቢንያም፡- የማመሰግነው በመጀመሪያ እግዚአብሄርን ነው፣ በመቀጠል ቤተሰቦቼን፣ የ12ኛ ክፍል ጓደኞቼን እንዲሁም በግቢ አብራኝ የምትማረውን ህይወት ወርቁን ለማመስገን እወዳለሁ።

ዓባይ፡- ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።

ቢንያም፡- እኔም አመሰግናለሁ!!

# የስኬታማ ተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ

## ‹‹የወደፊት ህልሜ ጎበዝ ኢንተርናሽናል የእግር ኳስ ዳኛ መሆን ነው››

ተማሪ ሞገስ ሞላ



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ ወር 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ሳይንስ አካዳሚ በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከአካዳሚው ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነው የስፖርት ሳይንስ /Physical Education/ትምህርት ክፍል ተማሪ በእንግድነት ይዘን ቀርበናል፡፡ ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታው፣ ስለአሳለፈው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ-ምልልስ አድርጋለች፡፡ መልካም ቆይታ !!

ዓባይ፡- ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆንህ በቅድሚያ እያመሰገንን ራስህን ለዓባይ አንባብያን ብታስዋውቅልን?

---:-በመጀመሪያ ይህን እድል ስለሰጣችሁኝ እጅግ በጣም እያመሰገንኩ ስሜ ሞገስ ሞላ ጌጤነህ እባላለሁ፤ የትውልድ ቦታዬ አማራ ክልል በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ወገራ ወረዳ ልዩ ስሙ አምባጊወርጊስ በሚባል ስፍራ ነው፡፡

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግህና የትምህርት ቤት ህይወትህ ምን ይመስል ነበር፤ እስቲ እንጨዋወት?

ሞገስ፡- የልጅነት አስተዳደጌ ለቤተሰቦቼ ታዛዥና ታላላቅ እህትና ወንድሞቸን አክባሪ ሆኜ፣ በገጠራማው ስፍራ ላሞችን እየጠበኩ፣ አትክልቶችን ውሃ እያጠጣሁ፣ ገበያ እየተላኩ ነው ያደኩት፡፡ የትምህርት ቤት ህይወቴ በጣም ጥሩና ደስ የሚል ነበር፤ ልጅ እያለሁ ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ስማር ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ በመያዝ አጠናቅቄ ከ9ኛ-12ኛ ክፍልም የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄአለሁ፡፡

ዓባይ፡- የዩኒቨርሲቲን ህይወት እንዴት ትገልፀዋለህ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርክበት ነገር ምን ይሆን?

ሞገስ፡- የዩኒቨርሲቲ ህይወቴ በጣም ደስ ይላል፤በ 4 ዓመት የዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ትንሿን ኢትዮጲያ በሚገባ አውቄአለሁ፡፡ ከተለያየ ቦታ የሚመጡ ተማሪዎች ጋር አብረን ዶርም እንይዛለን፣ በጋራ እንበላለን፣ ኳስ እንጫወታለን፣ የቡድን ስራ እንሰራለን፡፡ በዚህ ውስጥ ከተለያየ ቦታ የመጡ ተማሪዎችን ባህል፣ ወግ፣ ልምድ፣ ባህሪና የመሳሰሉትን ነገሮች ለማወቅ ችያለሁ፡፡

ዓባይ፡- የምን ትምህርት ክፍል ተማሪ እንደሆንክ እና እስካሁን ያለህ አማካይ ውጤት ስንት እንደሆነ ብትገልፅልን?

ሞገስ፡- በስፖርት ሳይንስ /Physical Education/ ተማሪ ስሆን ያለኝ አማካይ ውጤት 3.73 ነው፡፡

ዓባይ፡- የመምህራንን የማስተማር ብቃት እንዴት ታየዋለህ? ላንተ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትለው አስተማሪ ካለ ብታስተዋውቀን?

ሞገስ፡- የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመምህራን የማስተማር ብቃት በጣም ጥሩ ነው እላለሁ፡፡ ነገር ግን የተለያዩ አስተማሪዎች ከተለያየ ትምህርት ክፍል ሌላ ተጨማሪ ኮርስ ሲያስተምሩን የጊዜ መጣበብ ስለሚኖርብን እና አንድ ሴሚስተር በ45 ቀን የምንጨርስበት አጋጣሚም ስለነበር የሁሉንም መምህራን ብቃት ለይቶ ለማወቅ ይከብዳል፡፡ ይሁን እንጂ ለእኔ ውጤታማ መሆን ልዩ ቦታ ያላቸው መምህራን አሉ፡፡ ስማቸውን ለመጥቀስ ያህል ዶ/ር ዳኛቸው ንግሩ፣ ዶ/ር ሀይለእየሱስ ጌታቸው፣ ዶ/ር ጋሻው ተሰማ እና መምህር በውቀቱ ቸኮል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ዓባይ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ፤ በአንተ እይታ እንዴት ትገልፀዋለህ?

ሞገስ፡-ከላይእንደገለፅኩትየመጣደፋ ሁኔታ እየተለመደ ስለመጣ ለአንድ ሴሚስተር ከ2 ወር ጊዜ ያነሰ እየተሰጠው በሰሜስተር 7/8 የትምህርት ዓይነቶች እየወሰድን እና በ45 ቀን ውስጥ ሰሜስተሩ እየተጠናቀቀ እውቀት የሚለው ነገር ስለሚከብድ እንደተባለው ፈተና ተኮር ይመስለኛል፡፡

ዓባይ፡- በዩኒቨርሲቲው ቆይታህ ውጤታማ ለመሆን የምትከተለው የአጠናን ስልትህ ምን ይመስላል?

ሞገስ፡- ውጤታማ ለመሆን የምከተለው በክፍል ውስጥ መምህራን ሲያስተምሩ በደንብ እከታተላለሁ፣ አጫጭር ኖት(ማስታወሻ) እይዛለሁ፣ የግልም ይሁን የቡድን ስራ ሲሰጠን ከተለያዩ መረጃዎች በማንበብ በደንብ እሰራለሁ፣ አብዛኛው ተማሪ ከኢንተርኔት ያወረዱትን እርማት እንኳ ሳያደርጉና ሳይረዱት ለመምርራን ያስገቡታል፡፡ እኔ ግን በደንብ ስለማነበውና ስለምረዳው በፈተና ወቅትም ከተለያዩ ሞጁሎች እያጣቀስኩ ያነበብኳቸው ነገሮች በጣም ይጠቅሙኛል፡፡

ዓባይ፡- ለስኬትህ ሚስጥሩ ምንድን ነው?

ሞገስ፡- ለስኬቴ ሚስጥር ነው ብዬ የማስበው ጠንክሬ ማንበቤ፣ የቤተሰብንና የሃገርን አደራ አለመርሳቴ በአጠቃላይ አላማን አለመርሳት ነው፡፡

ዓባይ፡- ለዚህ ደረጃ እንድትደርስ ያደረገህ አርያ/ሞዴል የምትለው ማን ነው? ለምን?

ሞገስ፡- ለዚህ ደረጃ እንድደርስ ሞዴል ነው ብየ የማስበው ሰው ታላቅ ወንድሜ ነው፤ ብርሃኔ ሞላ ይባላል፡፡ እጅግ በጣም ጎበዝ ፣ብርቱና ምስጉን ጥሩ ባህሪ ያለው በስራ ባልደረቦቹ ተወዳጅ እና ሀገር ወዳድ ጠንካራ ሰራተኛ ነው፡፡ ስራን ከልቡ የሚሰራ ለሰው የሚያዝን ስለሆነ ከ9ኛ ክፍል ጀምሬ ዩኒቨርሲቲ እስከምገባ ድረስ አንድ ቤት ተከራይተን እንጀራና ዳቦ በመግዛት ወጥ እየሰራን እንመገብ ነበር፡፡ በየዕለቱ የምሰራውን ነገር ይከታተለኛል፡፡ ያስተካክለኛ፤ የተሻለ ደረጃ እንድደርስ የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

እኔ ልጅ እያለሁ በጣም አስቸጋሪ ስለነበርኩ ነው ከሱ ጋር ሆኘ ትምህርቴን እንድከታተልና ብዙ ነገሬ እንዲስተካከል ያደረገው፡፡ ከሱ ብዙ ነገር ነው ያገኘሁት፡፡ ለሁሉም ፈጣሪ ይመስገን ጥሩ ደረጃ ላይ መሆኔን ወንድሜ ሲያይ በጣም ደስተኛ ነው፡፡ ለቤተሰባችን የመጀመሪያ ልጅ ነው፣ እኔ ደግሞ 5ኛ ልጅ ነኝ፡፡ ከኔ በላይ ያሉት አንድ ወንድማችንና ሁለት እህቶቻችንን ተምረው የተሻለ ደረጃ እንደሚደርሱ የራሱን አስተዋፅኦ ስላደረገ አሁን ላይ የመንግስት ሰራተኛ ሆነው፣ ትዳር መስርተው፣ ልጅ ወልደው የተሻለ ስራ እየሰሩ ነው፤ የእሱ ትዳር ግን ቤተሰቦቹ ነን፡፡

ዓባይ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወትህ ምን ይመስላል?

ሞገስ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወቴ በጣም ደስ ይላል፡፡ የስፖርት ሳይንስ ተማሪ መሆኔ ከብዙ ተማሪዎች ጋር እንድተዋወቅ አድርጎኛል፤ ኳስ ሜዳም ብዙ ሰው ሊጫወት፣ ተቀምጦ ጨዋታ ሊያይና ሊዝናና ወይም ሊደግፍ ስለሚመጣ ከብዙዎች ጋር ተዋውቄአለሁ፡፡ ብዙ ተማሪዎች ስሜን ይጠሩኛል፡፡ ከሌላ ግቢ የኳስ ዳኛ እንድሆን ስለሚጋብዙኝ ሂጀ እዳኛለሁ፡፡ የልምምድ መስሪያ ቁሳቁስ ኳስን ጨምሮ በግሌ ስላለኝ ብዙ ተማሪዎች እንዳውሳቸው ሲጠይቁኝ እሰጣቸዋለሁ፡፡ እነሱም ሰርተው ሲጨርሱ አመስግነው ይመልሱልኛል፡፡ በሌላ በኩል የክፍላችን ተማሪዎች ተወካይ ስለሆንኩ ከብዙ መምህራን ጋር እንድቀራረብ አድርጎኛል፤ ከሁሉም መምህራን ጋር በሚያስብል ደረጃ በስልክም ሆነ በአካል እየተገናኘን ሃሳብ እንለዋጣለን፡፡ በዚህ መልኩ የግቢ ማህበራዊ ህይወቴ እጅግ በጣም ደስ ይላል፡፡ በተለይ ከኦሮሚያና ከደቡብ ክልል የመጡ ተማሪዎች በጣም ይወዱኛል፣ ያከብሩኛል፡፡ ስሜን በተደጋጋሚ እየጠሩ ሰላም ይሉኛል፡፡ እኔም ሁሉንም በእኩል አይን እያየሁ እወዳቸዋለሁ፡፡

ዓባይ፡- ድጋፍ የሚያደርግልህ ማን ነው? የገንዘብ እጥረትስ አጋጥሞህ ያውቅ ይሆን?

ሞገስ፡- እህትና ወንድሞቼ ስለሚያግዙኝ የገንዘብ ችግር ገጥሞኝ አያውቅም፡፡ እኔም ከሁሉም ዓይነት ሱስ ነፃ ስለሆንኩ ብዙ ገንዘብ አላጠፋም፡፡ በአጋጣሚ አልቆብኝ ለአንዳቸው ደውዬ ከተናገርኩ ከየአቅጣጫው ብዙ ብር ይልኩልኛል፤ ሳልደውል ዝም ስል እንኳ እነሱ ደውለው ብር አይቸግርህም ብለው ይጠይቁኛል፤ እኔ ግን ለመዝናናትም ሆነ ለመስራት ኳስ ሜዳ ስለምሄድ አላስፈላጊ ወጭ አላደርግም፤ ምናልባት ረጅም ጊዜ ኳስ ስለምጫወት ጫማ እጨርሳለሁ፤ ካልሲና ማሊያ በየቀኑ ስለማጥብ ብዙ ሳሙና ያስፈልገኛል፡፡

ወደ ገጽ 7 የዞረ

# የስኬታማ ተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ!

## ‹‹የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራን ጎበዞች ናቸው፤ያላቸውን ለመስጠት አይሰስቱም››

ተማሪ ቤዛ ፍቃዱ



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነችው የህግ ትምህርት ክፍል ተማሪ በእንግድነት ይዘን ቀርበናል፡፡ ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ፣ ስለአሳለፈው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ-ምልልስ አድርጋላታለች፡፡ መልካም ቆይታ !!

‹‹የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራን ጎበዞች ናቸው፤ያላቸውን ለመስጠት አይሰስቱም›› ተማሪ ቤዛ ፍቃዱ

ዓባይ፡- በቅድሚያ ለቃለ ምልልስ ፈቃደኛ ስለሆንሽልን እያመሰገንን ራስሽ ለዓባይ አንባብያን ብታስተዋውቂልን?

እኔም አመሰግናለሁ፡፡ ቤዛ ፍቃዱ እባላለሁ ተወልጄ ያደኩት አዲስ አበባ ነው፡፡

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግሽና የትምህርት ቤት ህይወትሽ ምን እንደሚመስል እንጨዋወት?

ቤዛ፡- መልካም፡፡ ያደኩት ከቤተሰቦቼ ጋር ነው፡፡ የትምህርት ቤት ህይወቴ ጥሩ የሚባል ትውስታ ነው ያለኝ፡፡

ዓባይ፡- ዩኒቨርሲቲን እንዴት ትገልጪዋለሽ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርሽበት ነገር ምንድን ነው?

ቤዛ፡- ዩኒቨርሲቲ ብዙ ነገር የሚያስተምርሽ ቦታ ነው፤ ከቤተሰብ ስትለያይ እንዴት በራስሽ ነገሮችን እንደምታከናውኚ የሚያሳይሽ ቦታ ነው፡፡ ከቀለም ትምህርት ባለፈ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ማህበራዊ ህይወትን ተምሬበታለሁ፡፡

ዓባይ፡- የመምህራን እና የማስተማር ብቃት እንዴት ታይዋለሽ? ላንቺ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትይው አስተማሪ አለ? እንዴት?

ቤዛ፡- የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራን ጎበዞች ናቸው፡፡ ያላቸውን ለመስጠት አይሰስቱም፡፡ ለኔ ሁሉም ውጤታማ እንድሆን ያደረጉኝ መምህሮቼ ናቸው፡፡ በዚሁ አጋጣሚም ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

ዓባይ፡- በዩኒቨርስቲው ቆይታሽ ውጤታማ ለመሆን የምትከተይው የአጠናን ስልትሽ ምን ይመስላል?

ቤዛ፡- እኔ የማደርገው አስተማሪ በክፍል ውስጥ ሲያስተምር በደንብ መከታተል እና ፈተና ሲቃረብ በደንብ በማንበብ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በክፍል ውስጥ ያስተማሩትን ስለሆነ ፈተና ላይ የሚያመጡት በክፍል ውስጥ መከታተል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ዓባይ፡- በህይወትሽ በአርዓያ የምትከተይው ማን ነው? ለምን?

ቤዛ፡- ለየት አድርጌ አርዓያ ብዬ የምወስደው ሰው የለም፡፡ ሰዎች ብዙ ጥሩ ነገሮች ስላሏቸው ከእነሱ እነርሱን መማር ነው የምፈልገው፡፡

ዓባይ፡- እስካሁን በውጤትሽ ስንት ነጥብ ነው ያስመዘገብሽው?

ቤዛ፡- እስከአሁን ከአንዱ ሴሚስተር በስተቀር 3.64 አስመዝግቤያለሁ፡፡

ዓባይ፡- የስኬትሽን ምስጢር አጫውችን እስቲ?

ቤዛ፡- ስኬት ምስጢር የለውም፡፡ ስኬት ስኬት የሚሆነው አጥብቀሽ ስትፈልጊው እና ለፈለግሽው ነገር ከልብሽ መስዋዕትነት ስትከፍይ ነው፡፡

ዓባይ ፡-በገንዘብም ሆነ በሃሳብ በቅርበት የሚያግዝሽ ማን ነው? የገንዘብ እጥረትስ አጋጥሞሽ ያውቃል ወይ?

ቤዛ፡- ቤተሰቦቼ ናቸው ድጋፍ የሚያደርጉልኝ፡፡ ከዩኒቨርስቲ የሚሰጠው ብር አነስተኛ ስለሆነ አብዛኛውን ጊዜ የገንዘብ እጥረት ያጋጥማል፡፡ ነገር ግን ቤተሰቦቼ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጉልኛል፡፡

ዓባይ ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወትሽ ምን ይመስላል?

ቤዛ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወት በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ ብዙ በተላመድሽ ቁጥር ቤተሰብ ትሆኛለሽ፡፡ ብዙ የምወዳቸው ጓደኞች አፍርቼበታለሁ፡፡

ዓባይ ፡- በህይወትሽ የገጠመሽ ፈተና ነበር? ካለ እንዴት አለፍሽው?

ቤዛ፡- እኔ ላይ ለየት ያለ ፈተና አላጋጠመኝም ግን ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚነሱ ረብሻዎች ትልቅ ፈተና ነበሩ፡፡ ያንን አልፌ ዛሬ እዚህ በመገኘቴ አምላኬን አመሰግናለሁ፡፡

ዓባይ ፡- ወደፊት ለኢትዮጵያ ምን ትመኛለሽ?

ቤዛ፡- ለኢትዮጵያ የምመኝላት አሁን ያለችውን ሳይሆን ሁላችንም በጭንቅላታችን ውስጥ ኢትዮጵያ ስትባል የምንስላትን እንድትሆን ነው፡፡

ዓባይ ፡- ማመስገን የምትፈልጊው አካል ካለ?

ቤዛ፡- በመጀመሪያ በሁሉም ነገር የረዳኝን እግዚአብሔርን እና እናቱን ድንግል ማርያምን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ከእነርሱ ቀጥሎ በብዙ ነገር የረዱኝን ቤተሰቦቼን እንዲሁም ጓደኞቼን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ዓባይ ፡-ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

ቤዛ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# የስኬታማ ተመራቂ ተማሪዎች ተሞክሮ!

‹‹እኔ የተማርኩት ጂኦሎጂ በመሆኑ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እጥረት ያለበትን የገጠሩን ህብረተሰብ በተማርኩት ሙያ የከርሰ ምድርን ውሃ በመጠቀም ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንዲጠቀሙ ማድረግ ምኞቴ ነው››፡፡ በጎሰው ይታያል



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከኮሌጁ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነችው የጂኦሎጂ ትምህርት ክፍል ተማሪ በእንግድነት ይዘን ቀርበናል፡፡

ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታው፣ ስለአሳለፈው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ-ምልልስ አድርጋለች፡፡ መልካም ቆይታ !!

‹‹እኔ የተማርኩት ጂኦሎጂ በመሆኑ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እጥረት ያለበትን የገጠሩን ህብረተሰብ በተማርኩት ሙያ የከርሰ ምድርን ውሃ በመጠቀም ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንዲጠቀሙ ማድረግ ምኞቴ ነው፡፡ ›› ተማሪ በጎሰው ይታያል

ዓባይ፡- በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆንሽ እያመሰገንን ራስሽን ለዓባይ አንባብያን ብታስተዋውቂልን?

---፡-ስሜ በጎሰው ይታያል እባላለሁ፤ የተወለድሁት በምስራቅ ጎጃም ደብረ ኤልያስ ወረዳ ነው፡፡

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግሽና የትምህርት ቤት ህይወትሽ ምን እንደሚመስል አጫውችን እስቲ?

በጎሰው፡- በልጅነቴ ከእህቴ ጋር ገጠር አሳርማን በሚባል ቀበሌ ነው ያደግሁት፡፡ በአሳርማ ከ1ኛ እስከ 6ኛ የተማርኩ ሲሆን ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ደግሞ ደብረ ማርቆስ ጤና እና ልማት ፀረ ወባ በተባለ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ነው የጨረስኩት፡፡

ዓባይ፡- ዩኒቨርስቲን እንዴት ትገልጭዋለሽ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርሽበት ነገር ምንድን ነው?

በጎሰው፡- ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ በኋላ በትምህርት ክፍለ ጊዜም ሆነ በግቢው የማገኛቸው ተማሪዎች ህብረ ብሄራዊነትን የተላበሱና በተለያየ የቤተሰብ ደረጃ እንደመምጣታቸው ከአካዳሚኩ እውቀት ተጨማሪ የህይወትን ተሞክሮ፣ ማህበራዊ ህይወትን የቀሰምኩበት ነው፡፡ ይህም ማለት ቋንቋ፣ ሐይማኖት፣ ብሄረሰብን በመገንዘብ የሰውን ባህሪ እንዴት ማወቅ እንዳለብን ተምሬበታለሁ፡፡

ዓባይ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ፡፡ ባንቺ በኩል እንዴት አገኘሽው?

በጎሰው፡- የመማር ማስተማር ሂደቱ እንደ ተማሪው ይወሰናል፡፡ አንዳንድ ተማሪ ለፈተና ያጠናል፣ አንዳንድ ተማሪ ደግሞ ለዕውቀት ያነባል፡፡ ስለዚህ በተማሪው አቅም ይወሰናል፡፡ በኔ እይታ የዩኒቨርስቲው የትምህርት አሰጣጥ ፈተና ተኮር ነው ብየ አላምንም፡፡ ትምህርት ተግባር ላይ ያተኮረ ቢሆን ይመረጣል፡፡

ዓባይ፡- የመምህራን እና የማስተማር ብቃት እንዴት ታይዋለሽ? ላንቺ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትይው አስተማሪ አለ? እንዴት?

በጎሰው፡- ከብዛታቸው አንጻር የተወሰኑት እየተዘጋጁ እና ሌላም አጣቃሽ መፅሀፍትን በመጠቀም የማስተማር ብቃታቸውን ለመተግበር ይጥራሉ፡፡ ጥቂቶችም ለረጅም ጊዜ የሚጠቀሙበትን ማንዋል እንዳለ ያስተምሩበታል፡፡

ዓባይ፡- በዩኒቨርስቲው ቆይታሽ ውጤታማ ለመሆን የምትከተለው የአጠናን ስልት ምን ይመስላል?

በጎሰው፡- የተለየ የአጠናን ስልት ባይኖረኝም ግቢ ከገባሁ ጀምሮ ማለትም መምህሩ ትምህርት ከሰጠበት ጀምሮ ከስር ከስር በማጥናት፤ ያልገባኝንም ከጓደኞቼ ከዛም አለፍ ሲል መምህራንን በማግኘት ያልገባኝን እረዳለሁ፡፡

ዓባይ፡- በህይወትሽ እንደ አርዓያ የምትከተይው ሰው ይኖር ይሆን? ካለ ለምን?

በጎሰው፡- ለኔ አርዓያ የሚሆነው ደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኘው ጤና እና ልማት ፀረ ወባ በተባለ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት የሚሰሩት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ክብር ዶክትሬት ያገኙት ዶ/ር አበረ ምህረቴ ሲሆኑ ለሰው ያለው አመለካከት የተቸገረን ሰው እንዴት መርዳት እንደሚቻል ተምሬባቸዋለሁ፡፡

ዓባይ፡- እስካሁን ያለሽ አማካይ ውጤት ስንት ነጥብ ነው?

በጎሰው፡- በጂኦሎጂ ትምህርት ዘርፍ 3.89 አስመዝግቤያለሁ፡፡

ዓባይ፡- ለስኬትሽ ምስጢሩ ምንድን ነው?

በጎሰው፡- ትምህርትን ለራሴ ብሎ ማሰብእናነገ ህይወቴንእቀይርበታለሁ ብሎ በማሰብ ትምህርትን መከታተል እንጂ የተለየ ሚስጢር የለኝም፡፡ አንዳንድ ተማሪ ተመርቆ መቀመጥ ነው ብሎ የሚያስብ አለ፤ እኔ ግን ህይወቴን እቀይርበታለሁ ብየ ስለማስብ ሁሌም ዝግጁ በመሆኔ ውጤቴም ስኬታማ ነው፡፡

ዓባይ፡- በሃሳብም በገንዘብም ድጋፍ የሚያደርግልሽ ማን ይሆን?

በጎሰው፡- አባቴ እንዲሁም ጤና እና ልማት ፀረ ወባ ድርጅት፤ ድርጅቱ በአካባቢው ነዋሪ ሁነው የተቸገሩና የተሻለ ውጤት ያላቸውን ሴቶችን ከምግብ እና አልባሳት በተጨማሪ በማስተማር ይረዳናል፡፡

ዓባይ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወትሽ ምን ይመስላል?

በጎሰው፡- ሀይማኖት፣ ፆታ እና ብሄር ሳይገድበኝ ከሁሉ ጋር ተግባቢ ነኝ ፡፡

ዓባይ፡- ወደፊት ለኢትዮጵያ ምን ትመኛለሽ?

በጎሰው፡- ሰላምን፤ እኔ የተማርኩት ጂኦሎጂ በመሆኑ ንፁህ የመጠጥ ውሃ እጥረት ያለበትን የገጠሩን ህብረተሰብ በተማርኩት ሙያ የከርሰ ምድርን ውሃ በመጠቀም ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንዲጠቀሙ ማድረግ ምኞቴ ነው፡፡

ዓባይ፡- ማመስገን የምትፈልጊው አካል ካለ?

በጎሰው፡- በቅድሚ እግዚአብሄርን አመሰግናለሁ፤ ቤተሰቤን እና ያስተማረኝን ጤና እና ልማት ፀረ ወባ ድርጅትን አመሰግናለሁ፡፡

ዓባይ፡- ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

በጎሰው፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡



# ‹‹ባለራዕዩ “አንድ ብር ከአንድ ዶላር ጋር እኩል እስኪሆን አልተኛም” የሚለዉ አባባል ይገዛኛል›› ተማሪ ተመስገን ኡፋይሳ ዶላ



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጅ ተቋም በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከተቋሙ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነው የቆዳ ምህንድስና ትምህርት ክፍል ተማሪ በእንግድነት ይዞን ቀርበናል፡፡

ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታው፣ ስለአሳለፈው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ-ምልልስ አድርጋለች፡፡ መልካም ቆይታ!!

‹‹ባለራዕዩ “አንድ ብር ከአንድ ዶላር ጋር እኩል እስኪሆን አልተኛም” የሚለዉ አባባል ይገዛኛል›› ተማሪ ተመስገን ኡፋይሳ ዶላ

ዓባይ፡- ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆንህ በቅድሚያ እያመሰገንን ራስህን ለዓባይ አንባብያን ብታስዋውቅልን?

ተመስገን፡- ስሜ ተመስገን ሁፋይሳ ዶላ ይባላል፡፡ የተወለድኩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ወላይታ ሶዶ ዞን ባይራ ኮይሻ ወረዳ ልዩ ስሟ ቡካማ ፌቂቃ ቀበሌ ነዉ፡፡

ዓባይ፡- የተመስገን የልጅነት አስተዳደግና የትምህርት ቤት ህይወት ምን ይመስላል?

ተመስገን፡- እንደማንኛዉም የገጠር ልጅ በሰፈር ተጫዉቼ ነዉ ያደኩት፡ ፡ 5ኛ ክፍል ስደርስ ቤተክርስቲያን ማገልገል ጀመርኩ፡፡እሱም ለትምህርቴ መጎልበት የራሱን አስተዋፅኦ አድርጎልኛል፡፡በልጅነቴ ወጣ ወጣ የምንል ልጅ አልነበርኩም፡፡

ዓባይ፡- ዩኒቨርስቲን እንዴት ትገልፀዋለህ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርክበት ነገር ምንድን ነው?

ተመስገን፡- ዩኒቨርሲቲ ማለት አንድ ሰዉ በእናቱ ማህፀን ዉስጥ ሲኖር ቆይቶ ሲወለድ ሌላ ህይወት እንደሚኖረዉ ሁሉ አንድ ልጅ ከቤተሰቦቹ ጋር ሲኖር ቆይቶ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲገባም እንደዚሁ የተለየ ህይወት ይኖራል ፡፡ ለኔ ዩኒቨርሲቲን የማየዉ እንደሱ ነዉ፡፡

ዓባይ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ፡ ፡ ባንተ በኩል እንዴት አገኘኸው?

ተመስገን፡- ፈተና ብዙ ነገርህን የምትገመገምበት ነዉ፡ ፡ እንደተባለዉ በብዛት ቲወሪ እንማራለን፡፡ የማሽነሪና የላብራቶሪ እጥረቶች ስላሉ በተግባር ትምህርቱ ላይ ክፍተቶች አሉ፤ሆኖም ሁለቱን አጣምሮ ለማስተማር የሚደረገዉ ጥረት በጣም ጥሩ ነዉ፡፡

ዓባይ፡- የመምህራንን የማስተማር ብቃት እንዴት ታየዋለህ? ላንተ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትለው አስተማሪ አለ? እንዴት?

ተመስገን፡- አንዳንድ መምህራን ውስንነት አለባቸዉ፤ ሌሎቹ ጎበዞች ናቸዉ፡፡ አንዳንዶች ያወቁትን ለማሳወቅ የሚጥሩ አሉ፡፡ ጎበዝ ሆነዉም ብዙም ትኩረት የማያደርጉ አሉ፡፡ ሁሉም መምህራን መመስገን አለባቸዉ፡ ፡ ለእኔ በተለየ ሁኔታ አቶ አለነ የሚባል የማሽን ድሮይንግ መምህር የተለየ ቦታ አለዉ፡፡ ሌሎችም በስም የማልጠቅሳቸዉ ብዙ መምህራን ለእኔ እዚህ መድረስ ብዙ ደክመዋልና አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ዓባይ፡- በዩኒቨርስቲ ቆይታህ ውጤታማ ለመሆን የምትከተለው የአጠናን ስልት ምን ይመስላል?

ተመስገን፡- የእኔ አጠናን ዘዴ አንድን ነገር ለማወቅ ብዙ ነገሮችን እፈትሻለሁ፤ የተሰጠኝንም ተግባር ቀድሜ እጨርሳለሁ፤ በፈተና ወቅትም የምችለዉን ያህል ዋጋ ከፍየ አነባለሁ፡፡

ዓባይ፡- በህይወትህ እንደ አርዓያ የምትከተለው ማን ነው? ለምን?

ተመስገን፡- በብዙ ቦታ አርዓያ የሚሆኑህ ሰዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ በትምህርት ቤት፣ በህይማኖት ተቋማት፣ በቤተሰብ ለእኔ ግቢ ዉስጥ አርዓያ የሆነኝ ናቲ የሚባል ልጅ ነዉ፡፡ በትምህርቱ ጎበዝ ስለነበር እንደ አርዓያ እወስደዋለሁ፡ ፡ በዚህ አጋጣሚ ናትናኤል ኮከብ ኮይራ በጣም አመሰግንሀለሁ፡፡

ዓባይ፡- ውጤት እንዴት ነው? እስካሁን ያለህ አማካይ ውጤት ስንት ነው?

ተመስገን፡- ቀጣዩን ሴሚስተር ባላውቀውም እስከአሁን ድረስ ባሉት ሴሚስተሮች 3.99 አስመዝግቤያለሁ፡፡

ዓባይ፡- ለስኬትህ ምስጢሩ ምንድን ነው?

ተመስገን፡- ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር አምናለሁ፡ ፡ ምንም ችግር ቢመጣ ለፈጣሪ እሰጣለሁ፡፡ ሌላዉ እናቴ ለስኬቴ ትልቅ ድርሻ አላት፤ ብዙ ዋጋም ከፍላለች፡፡ እሷን ሳስብ ብዙ ፍላጎቶቼን አቅባለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ በጣም አመሰግናታለሁ፡፡

ዓባይ፡- በሃሳብም በገንዘብም ድጋፍ የሚያደርግልህ ማን ነው? ከዚህ ጋር በተያያዘ ምን የምታጫውተን ጉዳይ ይኖራል?

ተመስገን፡- እንግዲህ ያው ክረምት ላይ ግቢ ሲዘጋ ስራ እሰራለሁ፡ ፡ የጎደለኝን ወንድሜ ያግዘኛል፡፡

ዓባይ፡- የግቢ ማህበራዊ ህይወትህ ምን ይመስላል?

ተመስገን፡- ግቢ ዉስጥ ጥሩ ማህበራዊ ህይወት አለኝ፡፡ ህይወትህ ላይ የሚመጡ ሰዎች አሉ፤ ከህይወትህ የሚወጡ ሰዎችም አሉ፡፡ ከምንም በላይ መከባበርና መተባበሩ በጣም ደስ ይላል፡፡

ዓባይ፡- በህይወትህ የገጠመህ ፈተና ነበር? ካለ እንዴት አለፍከው?

ተመስገን፡- በጣም የከፋ ነገር ገጥሞኝ አያዉቅም፡፡ የገጠር ልጅ ስትሆን የገንዘብ እጥረት ያጋጥምሀል፡ ፡ የገጠር ቤተሰብ አንድ ነገር ሸጦ ይሰጥሀል፤ በድጋሚ ለመጠየቅ ትፈራለህ፡፡ አፓረንት ሸፕ አዲስ አበባ ሄጄ ተቸግሬ ነበር፡፡ ከጓደኞቼ ጋር በመተባበር አልፈነዋል፡፡

ዓባይ፡- ወደፊት ለኢትዮጵያ ምን ትመኛለሽህ?

ተመስገን፡- ምኞት ብዙ ነዉ(ሳቅ)፡፡ ባለራዕዩ “አንድ ብር ከአንድ ዶላር ጋር እኩል እስኪሆን አልተኛም” የሚለዉ አባባል ይገዛኛል፡፡ እኔም አገሬ ተለዉጣ ማየት ነዉ ህልሜ፡፡ ሀገር ስታድግ ሁሉም ሰዉ ያድጋል፡ ፡ ለዚህ ሁሉ ወሳኙ ነገር ሰላም ነዉና የሀገሬን ሰላም እመኛለሁ፡፡

ዓባይ፡- በመጨረሻም ማመስገን የምትፈልገው አካል ካለ?

ተመስገን፡- በህይወቴ ብዙ የማመሰግናቸዉ ሰዎች አሉ፡ ፡ ቤተሰቦቼን፣ ቤተክርስቲያንን፣ መምህራንን እና ለህይወቴ መቃናት ድርሻ ያላቸዉን ሰዎች ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡

ዓባይ፡-ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

ተመስገን፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## ‹ዩኒቨርሲቲ ለቻሉበትና ላውቁበት ገነት፤ ላላወቁበት ግን ሲኦል ነው››
## ‹‹የትምህርት ስርዓቱም የማህበረሰቡን ባህል፣ ስርዓት፣ ትውፊትና ልማድ መሰረት ተደርጎ የተዘጋጀ አይደለም፡፡›› ተማሪ ሰለሞን አብርሃ



ሰላም ጤና ይስጥልን የተከበራችሁ የዓባይ ጋዜጣ አንባብያን፡፡ ዓባይ በነሐሴ 2014ዓ/ም እትሟ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ በ2014ዓ/ም ከሚመረቁ ተማሪዎች ከኮሌጁ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ተመራቂ የሆነው የጂኦግራፊ (ህብረተሰብ ሳይንስ) ትምህርት ክፍል ተማሪ በእንግድነት ይዘን ቀርበናል፡፡

ዓባይ ለተማሪያችን ስለዩኒቨርሲቲ ቆይታው፣ ስለአሳለፈው የስኬት ሚስጥርና ሌሎች ጥያቄዎችን በማቅረብ ቃለ-ምልልስ አድርጋለች፡፡ መልካም ቆይታ !

ዓባይ፡- በቅድሚያለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዓባይ ጋዜጣ ስም እያመሰገንን ስምህን እና የትውልድ ቦታህን ብትገልጥልን?

---- ፡- ሰለሞን አብርሃ ወርቅነህ እባላለሁ፡፡ የትውልድ ቦታዬ ራያ አላማጣ፣ ኮረም ወረዳ፣ ሙሴ ሰላም ቀበሌ ነው፡፡

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግህ እና የትምህርት ቤት ህይወትህ ምን እንደሚመስል ብታጫውተን?

ሰለሞን፡- አስተዳደጌ እንደማንኛውም የገጠር ልጅ በእረኝነት ስራ ነው ያደኩት፡፡ ወላጆቼ ወደ ትምህርት ገበታ እንድገባ ብዙም ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ ላንተ ትምህርት አያስፈልግህም ዝም ብለህ በጎችህን ጠብቅ ይቺን በግ ሰጥተንሃል፣ ለከርሞ ደግሞ ሌላ ትሰጣለህ፣ እያሉ ከትምህርት ማዕድ ሊያስቀሩኝ ፈልገው ነበር፡፡ይህ ሁሉ ባለማወቃቸውና በማህበረሰቡ ካለው የትምህርት እይታ የመነጨ ነበር፡፡ ነገር ግን እኔም ጓደኞቼ ሲማሩ አይቼ መማር እንዳለብኝ ለወላጆቼ ነገርኳቸው፣ እነሱም ትንሽ ለማባበል ቢሞክሩም የኔ ሀሳብ ግን ስላልተለወጠ በ1999 ዓ.ም ግዲ-ቆሎ በተባለ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንድገባ ተደረገ፡፡

ይህ ሲሆን እኔ የ10 ዓመት ልጂ ነበርኩኝ፡፡ የእኔ ወደ ትምህርት ቤት መግባት ተከትሎ ታናሽ ወንድሜ 3ኛ ክፍል ነበር ትምህርቱን አቋርጦ በጎችን ይጠብቅ ተባለ፡፡

እሱም እምቢ ብሎ ትምህርቱን ቀጠለ፡፡ በዓመቱ ግን አንተ ትንሽ ነህ ቀስ ብለህ ትማራለህ ተብሎ ትምህሩቱን አቋርጦ 2 ዓመት ሙሉ በጎችን ሲጠብቅ ኖረ፡፡ እኔም እንደሱ 3ኛ ክፍል ደረስኩኝ፡፡ ቆላ-ጽሐዲ ትምህርት ቤት የሚባል ት/ቤት ለኔ ትልቅ እድል ከፍቶልኛልና ደረጃየንም ማሻሻል ጀመርኩኝ፡፡ ከ1ኛ-3ኛ ክፍል 3 ደረጃ እየያዝኩ ነበር ያጠናቀኩት፡፡

ወደዚህ ትምህርት ቤት መጥቼ የ4ኛ ክፍል ትምህርቴን 2ኛ ደረጃ ይዤ አጠናቀቅኩኝ፡፡ ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ደግሞ 1ኛ ደረጃ በመያዝ እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ በአጠቃላይ ወይም በዩኒት 7ኛና 8ኛ ክፍል 1ኛ ደረጃ ይዤ ትምህርቴን በከፍተኛ ውጤት አጠናቅቄያለሁ፡፡ በመቀጠል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በኮረም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርቴን ተከታተልኩና በዚሁ ጊዜም ደረጃዬ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል በ1ኛ ነው ያጠናቀቀኩት፡ ፡ የ10ኛ ክፍል አገራዊ መመዘኛ ፈተና 3.00 ነጥብ በማምጣት ወደ 11ኛ ክፍል አለፍኩኝ፡፡

11ኛ እና የ12ኛ ክፍልም ውጤቱ ደህና ቢሆንም ደረጃዬ ግን 5ኛ እና 6ኛ ደረጃ ይዤ ነው ያጠናቀኩት፡ ፡ በመጨረሻም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና 375 በማምጣት ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገባሁ፡፡

ዓባይ፡- ዩኒቨርስቲን እንዴት ትገልፀዋለህ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርክበት ቁምነገር ምንድን ነው?

ሰለሞን፡- ለእኔ ዩኒቨርሲቲ ማለት አብዛኛዎቹ እንደሚገልጹት "ትንሿ ኢትዮጵያ" ናት፡፡ ምክንያቱም ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚመጡ ተማሪዎች ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚመጡ በመሆናቸው ስለ ዩኒቨርሲቲ ብዝኃነትን የምትማርበት፣ ኢትዮጵያዊነትን የምትረዳበት፣ አብሮነትን የምትለማመድበት ትልቅ የህይወት ምዕራፍ ነዉ፡፡ በዚህም አጋጣሚ የተለያዩ ቋንቋዎችን ለመማር ዕድል ይሰጣል፡፡ ከተለያየ ቦታ ብትመጣም የወንድማማችነት ስሜት እየተሰማህ እየተረዳዳህ እየተደጋገፍክ የምትኖረው የፍቅር አውድማ ነው ዩኒቨርሲቲ፡፡ እውነት ለመናገር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከተማርኩት የቀለም ትምህርት በላይ ብዙ የህይወት ትምህርት ቀስሜበታለሁ፡፡ ከሰው ጋር በሰላም የመኖር ጥበብ፣ ተግባቦት፣ መተጋገዝ፣ መንፈሳዊ ትምህርት በግቢ ጉባኤ፣ ማህበራዊ ኑሮ ወ.ዘ.ተ የህይወት ምንነት አስተምሮኛል፡፡ ዩኒቨርሲቲ ለቻሉበትና ላውቁበት ገነት፤ ላላወቁበት ግን ሲኦል ነው እላለሁ፡፡ በተለይ እዚህ ላይ ዕድሉ ከተሰጠኝ ማለፍ የማልፈልገው ነጥብ ላንሳ፡፡

በእርግጥ ዩኒቨርሲቲ ከላይ የገለጽኳውና ሌላ ብዙ ጥሩ ነገሮች ቢኖሩትም እንዳንድ መወገዝ ያለባቸው ኢትዮጵያዊ ማንነታችንም ጥላሸት የሚቀቡ ነገሮችም አሉ፡ ፡ ለምሳሌ፡- የዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎቻችን ማታ ማታ ወደ ጭፈራ ቤት የሚወጡበት ጉዳይ እንዲሁም አንዳንድ የሆቴል መኪናዎች ሳይፍሩና ተው የሚላቸው ስለታጣ ወደ ዩኒቨርሲቲው ግቢ ገብተው ሴት እህቶቻችን ጭነው የሚወስዱበት ጉዳይ ሳስበው ይከብደኛል፡፡ ምክንያቱም ልጆ እየተማረችልኝ ነው ብሎ የሚደሰት ወላጅ እንደዚህ ያለ ጉድ ከልጁ ሲሰማ ምን ይላል? ለዩኒቨርሲቲው የሚሰጠው ስምስ? ስለዚህ የዚህ ጉዳይ ማስተካከል የሚቻል ከሆነ ቢታሰብበት ጥሩ ነው እላለሁ፡፡

ዓባይ፡- አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንጂ እውቀት ተኮር ሆኖ አይታይም ይላሉ፡ ፡ ባንተ በኩል እንዴት አገኘሀው?

ሰለሞን፡- እውነት ነው! ግን የዚህ ጉዳይ ከላይ ብናመጣው የተሻለ ይመስለኛል፡፡ ከእሾሃማ ተክል መልካም ፍሬ የሚጠብቅ ማን ነው? ወጣቱ አዋቂና ተመራማሪ እንዲሆን በሀገራችን ምሁራን የተነደፈ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ይቅርና ዲፓርትመንት እንኳን የለም፡ ፡ ያሳዝናል! እኛ ኢትዮጵያዊያን በእርግጥ በጦርነት አልተሸነፍንም፤ በማንም አልተማረክንም፤ አልተገዛንም፣ ነጻነታችን አስከብረን ያለን ህዝቦች ነን፡፡ ነገር ግን ክላስ ውስጥ ተማርከናል፡፡

ነጮች በጦርነት አሸንፈው ባይገዙንም በትምህርት የማይታይ ቅኝ ግዛት እየገዙን ነው፡፡ አስተማሪውም ጥሎበት ሳይገባው ያስተምራል፣ ተማሪውም ፈተና በሚደርስበት ወቅት ብቻ ያጠናል፡፡

ሳይገባው ተመርቆ ይወጣል፡፡ የአንድ ተመራቂ ከፎቶው ስር ያነበብኩት ወደዚህ ላምጣው ‹‹ልመረቅ ስል ገባኝ፣ ሊገባኝ ስል ተመረኩኝ›› ይላል፡፡ ይህ ሁሉ እንዴት ሊሆን ቻለ ቢባል የትምህርት ስርዓቱ የማህበረሰቡን ባህል፣ ስርዓት፣ ትውፊትና ልማድ መሰረት ተደርጎ የተዘጋጀ አይደለም፡፡

ነገር ግን እንዲህ ስል ራሱን የቻለ ዕውቀትም እንደሚያስጨብጥ ሳልዘነጋ ነው፡፡

ዓባይ፡- የመምህራን እና የማስተማር ብቃት እንዴት ታየዋለህ? ላንተ ውጤታማነት ልዩ ቦታ አለው የምትለው አስተማሪ አለ? እንዴት?

ሰለሞን፡- በእኔ እይታ መምህራን ሁሉንም ባይሆን በተቻለ መጠን የያዙትን ዕውቀት ለማስጨበጥ ይጥራሉ፡፡ ለኔ ውጤታማነት ልዩ ቦታ ያላቸው መምህራን አዎ! አሉ፡፡ ከእነዚህም የመጀመሪያው መ/ር ግርማ በለው ይባላል፡፡

ይህ አስተማሪ አብዝቼ ከምወዳቸው አስተማሪዎቹ አንዱ ሆኖ በትምህርቱ ይህ ይጎድለዋል የማይባል እንዲሁም ለተማሪዎቹ በፀባይና ትህትና በተሞላበት የሚያስረዳ በምክርና በሀሳብ የሚደግፍ ቅን መምህር ነው፡፡

በተለይም ለእኔ ውጤታማነት ሁሌ የሞራል ድጋፍ በመስጠት ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው እንደ አርዓያ የምቆጥረው ነው፡፡ ሌላኛውም ዶ/ር ኤሊያስ ሲያስተምር በጣም ጎበዝና ለተማሪ አስፈላጊ ዕውቀት የሚያስጨብጥ ነው፡፡

ዓባይ፡- በዩኒቨርስቲው ቆይታህ ውጤታማ ለመሆን የምትከተለው የአጠናን ስልትህ ምን ይመስላል?

ሰለሞን፡- በእርግጥ የተለየ መርሀ-ግብር አውጥቼ አይደለም የማጠናው፡፡ የምከተለው የአጠናን ዘዴ መጀመሪያ (Course guide line) ስንሰጥ በዛ ውስጥ ያሉ ይዘቶች ከእነርዕሶቹ አነባለሁ፡፡

ከዛም አንድ ቀንሳላስተጓጉል ክላስ ላይ በስርዓት እያዳመጥኩኝ መዘክር እይዛለሁ፡፡

የጻፍኩትን ተመልሽ አነበዋለሁ፡ ፡ በመቀጠል አስተማሪ አስቀድሜ የተለያዩ Reference ኮርስ ጋይድ ላይ በማየት አጋዥ መጽሐፍት አነባለሁ፡፡

በመጨረሻም ለፈተና በማንብበት ጊዜ ብዙም አይከብደኝም፡፡ ውጤቱም ጥሩ ነው፡፡ በአጭሩ የአጠናን ዘዴዬ ይህንን ይመስላል፡፡

ወደ ገጽ 7 የዞረ

# እንኳን ለ2014 ዓ.ም የተማሪዎች የምረቃ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

